# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 199 መጋቢት 19 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!










# ከ100 ሺህ ሔክታር በላይ አሲዳማ መሬትን በማከም ምርታማነትን የማሳደግ ንቅናቄ ተጀመረ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ከ100 ሺሕ ሔክታር በላይ አሲዳማ መሬትን በማከም ምርታማነትን የማሳደግ ንቅናቄ በመላ ሀገሪቱ ተጀምሯል።

የ2016/17 ምርት ዘመን አሲዳማ መሬትን ለማከም የሚረዳ የግብርና ኖራ አቅርቦትና ስርጭት ሀገራዊ ማስጀመሪያ የንቅናቄ መርሐ ግብር ትናንት ተካሂዷል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ በመርሐ ግብሩ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፤ የሀገር ሕልውና የብዙ ጉዳዮች ድምር ውጤት ቢሆንም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ደግሞ የብዙ ችግሮች መፍትሔ ነው ብለዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የኑሮ ውድነት መቀነስ አጀንዳ ሲነሳ ምርትና ምርታማነት ላይ ትኩረት ማድረግን እንደሚጠይቅ ጠቅሰው፤ አጠቃላይ የአገር ኢኮኖሚና እድገት የሚመጣው ምርትና ምርታማነትን ማረጋገጥ ሲቻል ነው ብለዋል።

ከ100 ሺህ ሔክታር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






ወይዘሮ ሀናን ማሕሙድ

## «የረመዷን ኢፍጣር» የኢትዮጵያውያን አብሮነት ማሳያ

ገጽ 6

## ለውጭ ገበያ ከቀረበ ቡና ከ716 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

ገጽ 6

# ለዓባይ ግድብ ግንባታ በዚህ ዓመት ከ931 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል

- **በቦንድ ሳምንቱ 100 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዷል**
- **የግድቡን ቀሪ ሥራ ለማጠናቀቅ 50 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል**

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ስምንት ወራት ለዓባይ ግድብ ከ931 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ። በታላቁ ህዳሴ ግድብ የቦንድ ሳምንት 100 ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ መታቀዱንና የግድቡን ቀሪ ሥራ ለማጠናቀቅ 50 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግም ተመልክቷል።

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የህዳሴ ግድብ የቦንድ ሳምንትን አስመልክተው ለመገናኛ ብዙኃን ትናንት መግለጫ ሰጥተዋል።

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት የሚዲያ ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሃም በመግለጫቸው እንዳስታወቁት፤ በበጀት

ለዓባይ ግድብ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል








# ለ270 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች በውጭ ሀገራት የሥራ ዕድል ተፈጠረ

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የሥራ አጥነት ችግር ለመፍታት እየተሠራ ባለው ተግባር እስከ መጋቢት 12 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ለ270 ሺህ ለሚሆኑት ዜጎች በውጭ ሀገራት የሥራ ዕድል መፈጠሩን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ብርሃኑ አለቃ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ የሚስተዋለውን የሥራ አጥነት ችግር ለመፍታት እየተሠሩ ባሉት ሥራዎች በበጀት ዓመቱ እስከ መጋቢት 12 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስም ለ270 ሺህ ዜጎች በውጭ ሀገራት የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።



አቶ ብርሃኑ አለቃ

በ2016 በጀት ዓመት በሀገሪቱ የሚስተዋለውን የሥራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ እየተሠራ ካለው ሥራም አንዱ ዜጎችን በሕጋዊ መንገድ ወደ ውጭ ሀገራት ሄደው መብታቸው ተጠብቆላቸው ሥራ ሠርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ መሆኑን ጠቅሰዋል። በዚህም እስካሁን ድረስ ለ270 ሺህ ለሚሆኑት ዜጎች በውጭ ሀገራት የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል ብለዋል።

ወደ ውጭ ሀገራት ሄደው ለመሥራት የሚፈልጉ 900 ሺህ ዜጎች የኢትዮጵያ የሥራ ገበያ የመረጃ ሥርዓት መተግበሪያ ቴክኖሎጂን እየተጠቀሙ ነው ያሉት አቶ ብርሃኑ፤ እየተጠቀሙ ካሉት 900 ሺህ ሥራ ፈላጊዎች ውስጥ ለ270 ሺህ ዜጎች በውጭ ሀገራት የሥራ ዕድል እንደተፈጠረላቸው አስታውቀዋል።


በ2016 በጀት ዓመት ለ500 ሺህ ዜጎች የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ባለው ሥራም እስካሁን 270 ሺህ ዜጎች ወደ ዩናይትድ ዓረብ ኤሜሬት፤ ኳታር፤ ሳዑዲ ዓረቢያና ጆርዳን ሀገራት ሄደው የሥራ እድል ያገኙ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ከተላኩት 270 ሺህ ዜጎች ውስጥ 66 በመቶ የሚሆኑት ሳዑዲ ዓረቢያ፣ 25 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ዩናይትድ ዓረብ ኤሜሬት ድርሻውን እንደሚይዙም ጠቁመዋል።

ዜጎችን በውጭ ሀገራት የሥራ ስምሪት ተጠቃሚ ማድረጉ ጥራት ያለው የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፤ የዘመናዊ አኗኗር ልምድና ሥልጠና እንዲያገኙ ያግዛል፤ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ዜጋ ወደ ሥራ ለማሰማራት ይጠቅማል ሲሉ ተናግረዋል።

ዜጎች ወደ ውጭ ሀገራት በሥራ ተሰማርተው ገንዘብ በሕጋዊ መንገድ በባንክ ለቤተሰቦቻቸው ሲልኩም ሀገሪቱ በዓመት አንድ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ትችላለች ያሉት አቶ ብርሃኑ፤ የዜጎች የውጭ ሀገራት የሥራ ስምሪት ለሥራ አጦች የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ ሀገሪቱ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንድትሆን አስተዋፅዖ እንዳለው ጠቁመዋል።

በ2014 በጀት ዓመት 40 ሺህ፣ በ2015 በጀት ዓመት 120 ሺህ የሚሆኑ ዜጎች የውጭ ሀገር የሥራ እድል እንደተፈጠረላቸው ያስታወሱት አቶ ብርሃኑ፤ በ2016 በጀት ዓመት እስካሁን ለ270 ሺህ የሚሆኑ ዜጎች የውጭ ሀገራት የሥራ ስምሪት እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፤ ይህም ተጠናክሮም ይቀጥላል ብለዋል።



አቶ እንዳለ አሰፋ

## በኢኮኖሚ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወንጀሎችን የመከላከል ሥራ እየተሠራ ነው

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወንጀሎችን እንደ ጉዳታቸው መጠን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የመከላከል ሥራ እየተሠራ መሆኑን የፋይናንስ ደኅንነት አገልግሎት አስታወቀ።

በፋይናንስ ደኅንነት አገልግሎት የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ እንዳለ አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በወንጀል የተገኘ ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትና ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን በገንዘብ መደገፍን የመከላከልና መቆጣጠር ሥራ እየተሠራ ነው።

ከሐሰተኛ ገንዘብ ኅትመትና ልዩ ልዩ የማጭበርበር ሥራዎች፣ ከታክስ ስወራ፣ ተገቢውን ታክስ ካለመክፈል ጋር ተያይዞ የሚፈጸሙ ወንጀሎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

እንደ አቶ እንዳለ ገለጻ፤ በርካታ የማጣራት ሥራን የሚጠይቁና ከሥራው ባሕሪ አንጻር መግለጽ ባይቻልም እገታ፣ የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና ከኮንትሮባንድ ንግድ ጋር በተያያዘ በሕግ የተያዙ በርካታ ጉዳዮች አሉ። በተለይ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ በሚያደርሱት የጉዳት መጠን በመለየት በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የመከላከል ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ 22 የሚሆኑ ዋና ዋና ወንጀሎች መኖራቸውን ገልጸው፤ ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያና ቀጣናው ባሕሪ ጎልተው የሚታዩ ወንጀሎችን በመለየት የመከላከል ሥራ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

አቶ እንዳለ እንዳብራሩት፤ በ2016 በጀት ዓመት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀልን የመቆጣጠር ሥራ በስፋት ተሠርቷል። በርካታ ጉዳዮች ለሕግ አስከባሪ ተላልፈዋል። የገንዘቡን መጠን ለመግለጽ ቢቸግርም በቢሊዮን ገንዘብ መጠን ያለ ጉዳይ በሕግ ሂደት ላይ ነው።

የወጪና ገቢ ንግድን የተመለከቱ ወንጀሎች እንደሚገኙበት ጠቁመው፤ ነገር ግን ከሀገር ውጪ መረጃ የሚያስፈልጋቸው በመሆናቸው እነዚህን ወንጀሎች ወደ ሕግ ለማቅረብ ጊዜን የሚጠይቁ ናቸው ብለዋል።

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ በዓለም አቀፍ ደረጃ የጋራ ርብርብ የሚደረግበት መሆኑን ገልጸው፤ የጉዳቱ መጠን ሀገርንና ዜጎችን ከመጉዳቱ ባሻገር ድንበር ተሻጋሪ ጉዳት አለው። በወጪ ገቢ ምርትና የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ተፅዕኖ ያለው በመሆኑ ሁሉም ሀገራት ትኩረት የሰጡት ጉዳይ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ኅብረተሰቡ በዚህ ወንጀል የሚሳተፉ አካላት ሲያጋጥሙት ጥቆማ መስጠት እንዳለበትና ግለሰቦች ሳያውቁ ወደ ወንጀል ድርጊቶች እንዳይገቡም አቶ እንዳለ አሳስበዋል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ማብራሪያ፤ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ የፋይናንስ ሥርዓቱን ጤናማነትና የሀገር ሕልውና ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ለመከላከል ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በትብብር እየሠራን ነው። እንዲሁም ወንጀሎች በባሕሪያቸው ድንበር ተሻጋሪ በመሆናቸው ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በጋራ የሚሠሩ ሥራዎች እንዳሉ ገልጸዋል።

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል ምንጩ በርካታ ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ሙስና፣ ማጭበርበር፣ የታክስ ጥሰት፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና መሰል ወንጀሎች ተጠቃሽ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

የፋይናንስ ደኅንነት አገልግሎት ከባንኮችና ከተለያዩ አካላት ጥቆማዎች ሲደርሱት የማጥራትና የትንተና ሥራ በመሥራት ከተገኘው ውጤት በመነሳት ክስ ለሚመሠርት አካል እንደሚያስተላልፍ ገልጸዋል።



የሺእመቤት ደምሴ (ዶ/ር)



ወ/ሮ መሠረት ዳምጤ



ደረጀ እንግዳ (ዶ/ር)

# ዩኒቨርሲቲው ለግዢ ያወጣውን 163 ሚሊዮን ብር ማወራረድ እንደሚጠበቅበት ማሳሰቢያ ተሰጠው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ባለፉት ዓመታት ለግዢ ሠራተኞች እና ለእቃ አቅራቢዎች የከፈለውን ከ163 ሚሊዮን ብር በላይ በአስቸኳይ እንዲያወራርድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ።

ቋሚ ኮሚቴው የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የ2014 በጀት ዓመት የፋይናንስ ሕጋዊነት ኦዲት ሪፖርትን በትናንትናው እለት ገምግሟል።

በግምገማው ዩኒቨርስቲው ግዢ የፈጸመባቸው በርካታ ንብረቶች ቢኖሩም የግዢ ጨረታ ሰነድ አቅርቦ ሂሳብ አለማወራረዱ ተነስቷል። በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው በንብረት አያያዝና አመዘጋገብ እንዲሁም በስፖንሰርሺፕ የሚያስተምራቸው መምህራንን በገቡት ውል መሠረት መክፈል ያለባቸውን ክፍያ አለመፈጸማቸውን በኦዲት ሪፖርቱ ተመላክቷል።

በወቅቱ የቋሚ ኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ የሺእመቤት ደምሴ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ዩኒቨርስቲው ከኦዲት ግኝቱ በኋላ በድርጊት መርሐ ግብሩ የግዢ ሰነድ ማቅረብ ችሏል። ሆኖም ሰነድ ከማቅረብ ባለፈ ለዕቃ አቅራቢዎች የተሰጠ 163 ሚሊዮን 70 ሺህ 630 ብር እንዲሁም ለግዢ ሠራተኞች የተሰጠ 882 ሺህ 886 ብር በአስቸኳይ ሊወራረድ ይገባል።

ማወራረድ የማይቻለውን ገንዘብም ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ዩኒቨርስቲው መሥራት ይኖርበታል ያሉት ሰብሳቢዋ፤ የግዢ ጨረታ ሰነድ የተሰበሰበላቸው ጉዳዮችን ሂሳባቸውን በማወራረድ እስከ ግንቦት 30 ቀን ለዋና ኦዲተር ማቅረብ እንደሚገባው አሳስበዋል።

ሰብሳቢዋ፤ ከመምህራን ጋር በተገባ ውል መሠረት ዩኒቨርሲቲው በ2013፣ 2012 እና 2011 ዓ.ም ስምንት ሚሊዮን 359 ሺህ 744 ብር ያልሰበሰበው ገንዘብ እንዳለ በኦዲት ሪፖርቱ መመላከቱን ገልጸው፤ ዩኒቨርስቲው ይህን ገንዘብም በአስቸኳይ ሰብስቦ ወደ ካዝና ማስገባት አለበት ሲሉ አሳስበዋል።

ዩኒቨርሲቲው በንብረት አያያዝና አመዘጋገብ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት እንዳለበት አመልክተው፤ በተለይም በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋል የነበረባቸው 114 ቶነሮች ጊዜ ያለፈባቸው በመሆኑ ሊወገዱ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሠረት ዳምጤ እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው የኦዲት ግኝት አስተያየት መነሻ በማድረግ የሠራቸው ሥራዎች ለሌሎች ተቋማት አስተማሪ የሚሆኑ ናቸው። ብዙዎቹ የኦዲት ግኝቶች ላይ ዩኒቨርሰቲው የግዢ ሰነዶችን በማሟላት ማቅረብ ችሏል ብለዋል።

ዩኒቨርስቲው ከኦዲት ግኝቱ በኋላ የንብረት አያያዝና አመዘጋገብ ላይ የሠራው ሥራ ግን አናሳ ነው ያሉት ዋና ኦዲተሯ ፤ በተለይም የሚሠሩና የማይሠሩ ቶነሮች በአንድ ላይ የተቀመጡ በመሆናቸው ዩኒቨርስቲው ይህን በመለየት መወገድ ያለባቸውን ማስወገድ ይኖርበታል ሲሉ አሳስበዋል።

የዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት ደረጀ እንግዳ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የተፈጸሙ ግዢዎች በ2006 ዓ.ም መከናወናቸውን ገልጸው፤ ሆኖም ይህ ግዢ እንዳልተወራረደ ዩኒቨርሲቲው በተረዳ ጊዜ ኮሚቴ አዋቅሮ የግዢ ጨረታ ሰነዱን በማሟላት በአሁኑ ጊዜ ለዋና ኦዲተር ማቅረብ ተችሏል ብለዋል።

መምህራን መክፈል ያለባቸውን ክፍያ በተመለከተም እስካሁን 60 ሺህ ብር ተመላሽ ማድረግ ተችሏል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ቀሪዎቹን ለማስመለስ በሕግ ሂደት ላይ እንገኛለን ሲሉ ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንቱ፤ በግምጃ ቤት የሚገበኙ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ቶነሮች አሁን ላይ እየተወገዱ እንደሚገኙ ገልጸው፤ ሌሎች የዩኒቨርስቲውን ንብረቶች ለመቆጣጠርም ሲስተም ዘርግተን እየሠራን ነው ሲሉ ለቋሚ ኮሚቴው አብራርተዋል።



አቶ መስፍን ታደሰ

# የአካባቢ ጥበቃ

## ሕግ ራሱን የቻለ የሙያ ዘርፍ ሆኖ በዩኒቨርስቲዎች ሊሰጥ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን የአካባቢ ጥበቃ ሕግ ራሱን የቻለ የሙያ ዘርፍ ሆኖ በዩኒቨርስቲዎች እንዲሰጥ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አስታወቀ።

የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ሕግና ደረጃዎች ዴስክ ተወካይ ኃላፊ አቶ መስፍን ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚፈጸም ወንጀልን ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን የአካባቢ ጥበቃ ሕግ ራሱን የቻለ የሙያ ዘርፍ ሆኖ በዩኒቨርስቲዎች እንዲሰጥ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው።

በአየር ንብረት ለውጥና በአካባቢ ብክለት የሚያስከትሉ የአካባቢ ጥበቃ ወንጀሎች እያደጉ በመምጣታቸው ተጠያቂነትን በማስፈን ተገቢ መሆኑን ገልጸው፤ የወንጀል ምርመረውን ለማሳደግ፤ የመረጃ አሰባሰብን ለማጠናከር፤ ተጠያቂነትን ለማስፈን የአካባቢ ጥበቃ ሕግ ራሱን የቻለ ሙያ ሆኖ በዩኒቨርስቲዎች መሰጠት አለበት፤ ይህንንም ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

የአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚፈጸም ወንጀል የራሱ የሆነ ልዩ ባሕሪ ስላለው ወንጀሉን ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን በአካባቢ ጥበቃ ላይ ግንዛቤ ያላቸው የሕግ ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ ያሉት አቶ መስፍን፤ ይህንንም ለማድረግ የአካባቢ ጥበቃ ሕግ እንደ አንድ የሙያ መስክ በዩኒቨርስቲዎች እንዲሰጥ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል። በአካባቢ ላይ የሚፈጸም ወንጀልን ለመከላከልና ወንጀል የሚፈጸሙ አካላትን ተጠያቂ ለማደረግ የአካባቢ ጥበቃ ሕግ ሥርዓተ ትምህርት ተቀርፆለት በተወሰኑ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለማስጀመር የተጀመሩ ሥራዎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

የአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚፈጸም ወንጀልን ለመከላከል የፀጥታ አካላት ሚና ትልቅ ነው ያሉት አቶ መስፍን፤ የመረጃ አሰባሰብ አቅም ለማጎልበት በኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ የአካባቢ ጥበቃ ሕግ ከፖሊስ ማሠልጠኛ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ተካቶ እንዲሰጥ ተደርጓል፤ ፖሊሶችም ትምህርቱን ወስደው ወደ ሥራ ሲሰማሩ የአካባቢ ደኅንነት የሚጠብቁ ይሆናል ብለዋል።

በተጨማሪም የአካባቢ ጥበቃ ወንጀል የትምህርት ሥርዓት በኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ መሰጠቱ የፖሊሶች የምርምራና የመረጃ አያያዝ በትምህርት የተደገፈ እንዲሆን በማደረግ በአካባቢ ላይ ለሚፈፀም ማለትም ከደረጃ በላይ ድምፅ መጠቀምን፣ ኬሚካልን በአግባቡ አለማስወገድንና መሰል ወንጀሎች ለመከላከልና ተፈጸመው ሲገኙም ወደ ሕግ አቅርቦ ተገቢው ቅጣት ለማስቀጣት ትልቅ ዕገዛ ያደርጋል ሲሉ ገልጸዋል።

ዳኞች፣ ዐቃቤ ሕግና ፖሊሶች ስለአካባቢ ጥበቃ ሕግ በቂ ዕውቀት ሲኖራቸው ከመረጃ አሰባሰብ እስከ ፍትሕ አሰጣጥ ድረስ ያለውን ሂደት በትክክል እንዲረዱትና ተጠያቂነትን እንዲያሰፍኑ እንደሚያደርግም አመልክተዋል።

የአካባቢ ጥበቃ ወንጀልን ለመከላከል የአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚፈፀም ወንጀልን ብቻ የሚያስተናግዱ ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለማፀደቅ እየተሠራ መሆኑን በቅርቡ መዘገባችን የሚታወስ ነው።

# የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ምዝገባ በኦንላይን ተጀመረ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ መታወቂያ ካርድን በኦንላይን ተመዝግቦ ማግኘት እንደሚቻል የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም አስታወቀ። በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት በኩል ካርዱን ካሉበት ቦታ የማድረስ ሥራ መጀመሩንም ገልጿል።

በብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አቤኔዘር ፈለቀ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ የሕትመት ሥራ በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ሲከናወን ቆይቷል። የብሔራዊ መታወቂያ ካርዱን ማግኘት የሚፈልጉ ዜጎችም አገልግሎቱን ለማግኘት በአካል መገኘት ይኖርባቸው ነበር።

አሁን የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ለማግኘት ግዴታ በአካል መገኘት አያስፈልግም ያሉት አቶ አቤኔዘር፤ ዜጎች አገልግሎቱን በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ የኦንላይን ምዝገባ ተጀምሯል። የክፍያ ሥርዓቱም በቴሌ ብር እና በባንክ መክፈል እንደሚቻል ጠቁመዋል።

የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ማግኘት የሚፈልጉ ዜጎች card-order.fayda.et ድረ ገጽ ላይ በኦንላይን መመዝገብ እንደሚችሉ የገለጹት አቶ አቤኔዘር፤ ከዚህ ባለፈ በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት በኩል ካርዱን ካሉበት ቦታ እንዲመጣላቸው ማዘዝ እንደሚችሉ ተናግረዋል። ይህ አገልግሎት በተለይ በክፍለ ሀገር የሚኖሩ ዜጎችን ተደራሽ ያደርጋል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ነዋሪዎችም ካርዱን ካሉበት ቦታ ማግኘት ይችላሉ ያሉት አቶ አቤኔዘር፤ ዜጎች የብሔራዊ መታወቂያ




ካርድ የኦንላይን ምዝገባ ከማድረጋቸው በፊት የፋይዳ ቁጥራቸውን የሚገልጽ የጽሑፍ መልዕክት በስልካቸው የተላከ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚኖርባቸው ተናግረዋል።

እንደ አቶ አቤኔዘር ገለፃ፤ ከዚህ በፊት የነበረው የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ አሰጣጥ በአካል መገኘት የሚጠይቅ በመሆኑ ካርዱን ማግኘት የሚፈልጉ በርካታ ዜጎች በአንድ ቦታ እንዲገኙ አድርጓል። ይህም ረጅም ሰልፍ እንዲሁም ካርድ ሳይወስዱ የሚመለሱ ዜጎች እንዲበራከቱ አድርጓል። አሁን የተጀመረው የአሠራር ሥርዓት ይህንን ችግር ይቀርፋል።

በተመሳሳይ ነጋዴዎች እና ግብር ከፋዮች ይህንን የኦንላይን ምዝገባ ሥርዓት መጠቀም ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ የንግድ ፍቃድ በሚሰጡባቸው ቦታዎች የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ባለሙያዎች እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

እንደ አቤኔዘር ገለፃ፤ በአዋጁ መሠረት የመታወቂያው ትክክለኛ መጠሪያ የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ነው። ይህንን መታወቂያ እውን ለማድረግ እስከ አሁን ሦስት አሠራሮች ተዘርግተዋል። አንደኛው በኪስ የሚያዝ የፕላስቲክ መታወቂያ ሲሆን ሁለተኛው በፒዲኤፍ የተዘጋጀ ነው። ሦስተኛው በስልክ ላይ መታወቂያውን በማስቀመጥ መገልገል የሚቻልበት ሥርዓት ነው።

ሦስቱ አማራጮች በሕግ ፊት እኩል ተቀባይነት አላቸው። ይህንን በሚመለከት ለፖሊስ፣ ለክልሎች እና ለተለያዩ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት አቶ አቤኔዘር፤ ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ በኪስ የሚያዝ ወረቀት ብቻ ሳይሆን የራሱ መለያ /ፋይዳ/ የሚባል ቁጥር ይዞ በማንኛውም ቦታ በቁጥሩ ምክንያት አገልግሎት ማግኘት የሚያስችል ዘመናዊ አሠራር መሆኑን አስረድተዋል።

ዲጂታል መታወቂያ በኢትዮጵያ የሚኖር ማንኛውም ዜጋ የራሱን ማንነት የሚገልጽበት መለያ ነው ያሉት ያሉት አቶ አቤኔዘር፤ አንድ ሰው ከቤቱ ሆኖ የባንክ አካውንት መክፈት፣ የኢንሹራንስ አገልግሎት ማግኘትና በአገልግሎት ሰጭውና ተቀባዩ ዘንድ መተማመን መፍጠር የሚያስችል ነው ብለዋል።

በ2016 ዓ. ም ማብቂያ ለ25 ሚሊዮን ዜጎች የብሔራዊ መታወቂያ ፋይዳ ቁጥር ለመስጠት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ አቤኔዘር፤ እስከ አሁን ከሦስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የብሔራዊ መታወቂያ ፋይዳ ቁጥር እንደተሰጠ ገልጸዋል።

በ2018 ዓ. ም ማብቂያ ከ90 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የብሔራዊ መታወቂያ ፋይዳ እንዲኖራቸው ይደረጋልም ብለዋል።

# ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የኃይል አቅርቦት፣ የጋራጅና የፓርኪንግ ማበረታቻዎች ሊሰጣቸው ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የኃይል አቅርቦት፣ የጋራጅና የፓርኪንግ ማበረታቻዎችን ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ በርኦ ሀሰን የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ማብራሪያ፤ በሀገሪቱ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ለማስፋፋት መንግሥት የተለያዩ ማበረታቻዎችን እያደረገ ይገኛል።

ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የኃይል አቅርቦት፣ የጋራጅና የፓርኪንግ ማበረታቻዎችን ማድረግ በተመለከተ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ ያሳያል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በኢትዮጵያም ማበረታቻዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ሰነዶችን በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

በሀገሪቱ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች እንዲስፋፉ መንግሥት ከቀረጥ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ማበረታቻዎችን ማድረጉን ገልጸው፤ ሙሉ በሙሉ ከውጭ ሀገር ተገጣጥመው ለሚገቡ 15 በመቶ፣ በከፊል ተገጣጥመው ለሚገቡ አምስት በመቶ እና ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ የሚገጣጠሙ ከሆነ ከቀረጥ ነፃ የማድረግ ሥራ መሠራቱን አስታውቀዋል።

የቀረጥ ማበረታቻው በነዳጅ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ላይ ከሚጣለው ታክስ ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ በመሆኑ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በሀገሪቱ ለማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው ብለዋል።

እንደ አቶ በርኦ ገለጻ፤ መንግሥት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ለማስፋፋት ባደረገው የቀረጥ ማበረታቻ ከውጭ የገቡና በሀገር ውስጥ የተገጣጠሙ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከ100 ሺህ በላይ ደርሷል ብለዋል።

መንግሥት ያደረገው የቀረጥ ማበረታቻ የባለሀብቱን



ተነሳሽነትና የሀገሪቷን የታዳሽ ኃይል አቅርቦት ለማሳደግ እንዲሁም የአየር ብክለትን ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ እንደሚረዳም ተናግረዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ለአካባቢ እና ለማኅበረሰብ ጤናማ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችሉ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በ10 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ አረንጓዴ ትራንስፖርት ተግባራዊ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ሀገሪቱ ለነዳጅ ግዥ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ መቀነስ መቻላቸው እና ለአየርና የድምፅ ብክለት መንስኤ ባለመሆናቸው ተመራጭ ያደርጋቸዋል ብለዋል።

ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የጥገና እና የቻርጅ መሙያ ማዕከላት እጥረትን ለመቅረፍ እስካሁን ድረስ በአዲስ አበባ 60 የቻርጅ መሙያ ማዕከል መገጠማቸውን ገልጸው፤ በ10 ዓመት በአዲስ አበባ አንድ ሺህ 176 በክልል ከተሞች ደግሞ አንድ ሺህ 50 የቻርጅ መሙያ ማዕከላትን ለመገንባት ታቅዷል ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በ10 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ 148 ሺህ የቤት አውቶሞቢሎች እና 48 ሺህ 555 አውቶቡሶችን ወደ ሀገር ለማስገባት አቅዶ እንደነበር አስታውሰው፤ እቅዱ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት እየተሳካ በመሆኑ እና መንግሥት ለጉዳዩ በሰጠው ትኩረት 439 ሺህ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ለማስገባት እና ሁለት ሺህ 335 የኃይል መሙያ ማዕከል ለመገንባት እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ባለ ሃብትነት - መርሑ ታማኝነት፣ መገለጫውም ባለጸግነት ነው

ሃብት መልኩ ብዙ፣ ዓውዱም ልዩ ልዩ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያውያን ብሂልም ሆነ በሌሎች ማኅበረሰቦች እንዳለው እይታ የየራሱ መከሰቻም፤ መገለጫም አለው፡፡ ለአንዳንዱ ሃብት ገንዘብ ነው፤ ለሌላው ደግሞ ሃብት ጤና ነው፡፡ በሌላውም ሌላ መልክ አለው፡፡ ባለሃብትነትም እንደዛው እንደየማኅበረሰቡ የእሳቤ ዓውድ የሚለያይ ነው፡፡

ይሁን እንጂ አንድ ሃገር በሃብቷ ስትገለጽ፣ ከኢኮኖሚዋ ጋር የመቆራኘቱ ጉዳይ እውነት ነው፡፡ ባለሃብትነት እንደ ሃገር፤ ባለሃብትነት እንደ ማኅበረሰብ፤ ባለሃብትነት እንደ ግለሰብ ሲገለጽም በዚሁ መልኩ ካለው የኢኮኖሚ አቅም ጋር የሚተሳሰር ይሆናል፡፡

በዚህ ረገድ ባለሃብትነት ደረጃ እና መልኩ ይለያይ እንጂ፤ ከኢኮኖሚ አቅም፣ ገንዘብ ከማንቀሳቀስና ለሀገር ብሎም ለሕዝብ የሚሆን ወረት ከመፍጠር አኳያ ያለው እውነት ከሀገር ሀገር የተለያየ ገጽታ አለው፡፡

የሀገራት እድገት ከማኅበረሰቦች የሥራ እና የባለሃብትነት ደረጃ ጋር የመተሳሰሩን ያህል፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በድሃ ሀገር ውስጥ ቁጥራቸው ያነሰም ቢሆን የሃብት ማማ ላይ የተሰቀሉ ግለሰቦችን ማየት የተለመደ ነው፡፡

እነዚህ የባለሃብትነት መከሰቻ ተቃርኖዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ዋናው ጉዳይ ይሄ የግለሰቦች አልያም የቡድኖች ሃብት ለሀገር ብሎም ለማኅበረሰብ ጥቅምና እድገት አቅም የመሆን አለመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ባደጉት ሀገራት እነዚህ ባለሃብቶች ሃብታቸውን በማንኛውም አግባብ ከሀገር እና ሕዝብ ጥቅም ውጪ እንዲሆን አያደርጉም፡፡ ይሄን ማድረጋቸውም ለእነሱ ክብርን የሚያላብስ፤ ለሀገራቸውና ሕዝባቸውም የብልጽግና አቅምን የሚያጎናጽፍ ሆኗል፡፡

በአንጻሩ እንደ አፍሪካ ባሉ የሃብታም ደሃ ሀገራት ያሉ ባለሃብት ነን ባዮች ደግሞ፤ አንድም የሃብት ምንጫቸው በወጉ የማይታወቅ፤ ሁለተኛም ይሄንኑም ቢሆን ለሀገርና ሕዝብ ጥቅም እንዲሰጥ ከማድረግ ይልቅ፤ ከሀገር ማሸሽ እና ለራሳቸው የተቀናጣ ሕይወት ብቻ የመጠቀም አካሄዶች የተለመዱ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያም ያለው ሁነት ከዚህ ብዙም የተለየ አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለይም ከለውጡ ማግስት በተሠሩ ሥራዎች፤ ባለሃብቶች ሃብታቸውን ከማሸሽ ይልቅ ለሀገርም ለሕዝብም ጥቅምና አቅም በሚሆን መልኩ እንዲሠሩበት የማድረግ ጅምሮች ታይተዋል፡፡

ይሄ ጅምር ባለሃብቱ ያለውን ገንዘብ በተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ እንዲያውል፤ በዚህም የሥራ እድል እንዲፈጥር፣ የኢንዱስትሪውን ምርታማነት እንዲያሳድግ፣ የሕዝቦችን ተጠቃሚነት በሚያሳድጉ መስኮች ላይ ሠርቶ ለራሱም ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ እየተቻለ ነው፡፡

ይሄ ደግሞ ቀደም ሲል በተበላሹ የቢሮክራሲ አሠራሮች ምክንያት የተማረረው እና ላልተገባ የሙስናና ሌሎችም አካሄዶች ራሱን አጋልጦ የነበረው ባለሃብት፤ ከዚህ አይነት አካሄድ ራሱን እንዲያገልል እና በታማኝነት ሃብቱን ለኢንቨስትመንት እንዲያውል፤ ከትርፉም ተገቢውን ግብር እንዲከፍል የሚያደርገውን መልካም አጋጣሚ አስገኝቶለታል፡፡

መንግሥትም ይሄን እድል ተጠቅመው ወደ ልማቱም፣ ወደ ታማኝ ግብር ከፋይነቱም የተቀላቀሉ ባለሃብቶችን፤ ስለ መልካም ተግባርና ታማኝነታችሁ አመሰግናለሁ ሲል እውቅና በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ይሄም ባለሃብቱ የተሻለ መነሳሳት እንዲፈጠርበት አድርጓል፤ ባለው ሃብትም ለሀገርና ሕዝብ ሠርቶ አቅም የሚሆንበትን የተሻለ ምሕዳርም ፈጥሮለታል፡፡

ይሄ በታማኝነት ቅኝት የተገለጸው የባለሃብቶች መንገድ ታዲያ፤ በሂደት የተሰጣቸው ሃብት አንዱ የሀገር እና ሕዝብ ማገልገያ ስጦታ ፀጋቸው መሆኑን ወደ መገንዘብ አሸጋግሯቸዋል፡፡ ምክንያቱም የእነሱ ሕዝብን ማገልገያ፣ ሀገርን መታደጊያ፣ ለወጣቱም ተስፋ መፍጠሪያ አቅምና ፀጋቸው የተሰጣቸው ሃብት ነው፡፡

በመሆኑም ይሄን ሃብታቸውን አንደኛ፣ ከሙስናና ሌላም አሠራር በራቀ መልኩ መፍጠርን፤ ሁለተኛ፣ ካገኙት ሃብት ላይ በታማኝነት ግብር መክፈልን እና የመንግሥት አቅም መሆንን፤ ሦስተኛ፣ ለሕዝቡ ተጠቃሚነት፣ በተለይም ለወጣቱ የሥራ ዕድል ፈጠራ አቅም በሚሆን አግባብ ሃብታቸውን ለላቀ የሃብት መፍጠሪያነት ማዋልን መርሐቸው እያደረጉ መጥተዋል፡፡

በዚህ ረገድ ከሰሞኑ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እነዚህን በታማኝነት መርሕ ተጉዘው፣ በባለጸግነት የተገለጡ ባለሃብቶችን በጽሕፈት ቤታቸው አነጋግረው ነበር፡፡ በወቅቱም የባለሃብቱ ታማኝ ሆኖ ግብር መክፈሉ፤ ያለውንም ሃብት ለሀገርና ሕዝብ በሚሆን አግባብ ፈሰስ ማድረጉ፤ ለብልሹ አሠራሮችና ሙስና የሚጋለጥበትን ዕድል መቀነስ መቻሉ የሚያስመሰግነው ተግባር ስለመሆኑ ተነስቷል፡፡

በተመሳሳይ አሁንም ከዚህ በላቀ መልኩ አቅምን ለልማት ማዋል፤ የታማኝነት መርሕን መላበስ፤ ያካበቱት ሃብት የሕዝብና ሀገርን ማገልገያ እንዲሆን የተሰጣቸው ፀጋ መሆኑን ከልብ አምነው በዚሁ አግባብነት መሥራት እንደሚገባቸውም ማሳሰብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ባለሃብቱ፣ ሃብቱን ያገኘው ከሃገር፣ እንዲያውል የሚጠበቀውም ለሃገር መሆኑን በመገንዘብ፤ በታማኝነት ተጉዞ፣ በባለፀግነት/አገልጋይነት ተገልጦ ለሀገርም፣ ለሕዝብም የብልጽግና ጉዞ አቅም ሊሆን ያስፈልጋል፡፡


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዓባይ ገመዱ

ሚሊዮን ሺበሺ

**ሽረ ልጅ ሽረ ልጅ**
**ሽረ ልጅ ገመዱ**
**ቤትማ ምን ይሳል ዘግተውት ቢሄዱ**

የሚል የቃላዊ ግጥም ሀገርኛ ብሂል አለ። የሥነ ቃሉ መልዕክት፤ ልጅ ከተወለደ ባልና ሚስት አይፋቱም፣ እናትም አባትም የመኖር ጉጉት ይኖራቸዋል፤ ከራሳቸው በላይ ለልጃቸው ስለሚያስቡ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር አለ.... ለማለት ነው፡፡ በልጅ ገመድ ተሳስረዋል ለማለት ነው፡፡

ይህ የቃላዊ ግጥም ሀገርኛ ብሂል ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ያስታውሰኛል፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የመላው ኢትዮጵያውያን ልጅ ሆኗል፤ መላው ኢትዮጵያውያንን የሚያስተሳስር ገመድ ሆኗል፡፡ የጋራ ልብ እና የጋራ ሳምባ ሆኗል። ለምሳሌ፤ የተለያዩ የኀብረተሰብ ክፍሎች እና በተለያየ ጎራ ያሉ ምሑራን ሲናገሩ የጋራ ጉዳይ የሚጠቅሱት ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ነው። ‹‹የጋራ ጉዳዮቻችን›› ሲሉ ምሳሌ የሚያስቀምጡት የህዳሴውን ግድብ ነው። የእገሌ የሚባል ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያ የሚባል የጋራ ጉዳይ ነው፡፡

> **ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አሁን ያለውን ትውልድ ብቻ ሳይሆን በሕይወት የሌሉትን ሁሉ አንድ ያደረገ ነው**

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አሁን ያለውን ትውልድ ብቻ ሳይሆን በሕይወት የሌሉትን ሁሉ አንድ ያደረገ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ (በተለይም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ልማድ) መንግሥት በተተካካ ቁጥር ያለፈውን ሥርዓት መውቀስ የተለመደ ነው፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግን ይህን ልማድ ሁሉ የሻረ፣ ያለፈውን ትውልድ ሁሉ ያስተሳሰረ ገመድ ነው፡፡ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴን ከአቶ መለስ ዜናዊ፣ አቶ መለስ ዜናዊን ከዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጋር ያስተሳሰረ ገመድ ነው፡፡ ያን ትውልድ ከዚህ ትውልድ ጋር በቅብብሎሽ ያስተሳሰረ ነው፡፡ ያሰቡትም፣ ያስጀመሩትም፣ ያስፈጸሙትም በአንድ ገመድ እንዲተሳሰሩ አድርጓል፡፡

የዓባይ ግድብ አንድ የጋራ ጉዳይ ሆኖ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ጓዳ ጎድጓዳ ነካክቷል። ተማሪው ለደብተር ከሚሰጠው ላይ አዋጥቷል፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ከካፍቴሪያ ምግቡ ላይ ቀንሶ አዋጥቷል፡፡ ይህ በማንም ሰው ልብ ውስጥ የሚረሳ አይሆንም። ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የተገነባው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡ እዚህ ላይ በ2004 ዓ.ም አካባቢ በብዙ መገናኛ ብዙኃንና በማኅበራዊ ገጾች አጀንዳ ሆኖ የነበረ የአንዲት እናት ነገር ይጠቀሳል፡፡

በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ክልል ውስጥ ነው፤ ሕዝቡ አቅሙ የቻለውን ሁሉ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እያዋጣ ነው፡፡ አንዲት ድሃ ሴትዮ ይህን ነገር ያያሉ፡፡ ድሃ ናቸው በሚል ማንም አልጠየቃቸውም፡፡ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች ሲያዋጡ አስተዋሉ፡፡ ጉዳዩም ለዓባይ ግድብ መሆኑን ሰሙ። እኚህ ሴትዮ በቀጥታ ወደ አስተባባሪዎች ነበር የሄዱት፡፡ በቤታቸው ውስጥ ያለው ንብረት አንዲት ዶሮ ነበረች፡፡ ያቺን ዶሮ ይዘው የበኩሌን ካላዋጣሁ አሉ፡፡ ‹‹ግዴለዎትም!›› ቢባሉም ‹‹በዓባይ ግድብ ላይ እጄ መኖር አለበት›› አሉ፡፡ የሴትዮዋ ዶሮ ተወሰደች፤ ተወስዳ ዶሮዋ በጨረታ ተሸጠች፡፡ በጨረታው የተገኘው ገቢ ከአካባቢው ከተሰበሰበው ይበልጥ እንደነበር ክስተቱን የተከታተለ በወቅቱ ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ይሠራ የነበረ ጋዜጠኛ ሲያወራ ሰምቻለሁ፡፡

እዚህ ላይ ብዙ ነገር እንረዳለን፡፡ ሴትዮዋ በዓባይ ጉዳይ ላይ የቤታቸውን የመጨረሻ ገንዘብ የሆነችውን ዶሮ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ታሪካዊ ዐሻራ ላይ እጄ ይኑር ብሎ ማሰብ ትልቅ ብልህነት፣ አርቆ አስተዋይነትና ፍልስፍና ነው፡፡ ወዲህ ደግሞ የኢትዮጵያውያንን ሥነ ልቦና ያሳያል፡፡ ኢትዮጵያዊ አቅሙ በቻለ ሁሉ ይታገላል እንጂ እኔ አልችልም ብሎ አይቀመጥም። እኚህ ባለ አንድ ዶሮ ሴትዮ ከኢንቨስተሮች እኩል የተሳትፎ ድርሻ አላቸው፡፡ ዓባይን ከዓድዋ ድል ጋር የምናመሳስለውም ለዚህ ነው፡፡ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ ሁሉም በመደፈር ስሜት በነቂስ እንወጣው ሁሉ፤ እኚህ ሴትዮም ‹‹ባለ ሀብት ይሳተፍ›› ብለው ዝም አላሉም፡፡ ዓባይ የኢትዮጵያውያን ገመድ ነው ስንል ማሳያዎቻችን እነዚህ ነገሮች ናቸው፡፡

የዓባይ ግድብ እነሆ 13 ዓመታት ሆኑት፡፡ በእነዚህ 13 ዓመታት ውስጥ የተለያዩ የፖለቲካ ሁነቶች ተከናውነዋል፡፡ ከ2008 ዓ.ም እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በኦሮሚያና አማራ ክልል ውስጥ መረር ያሉ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ነበሩ፡፡ ከ2010 ዓ.ም የለውጡ መንግሥት ከመጣ በኋላ የሰሜን ኢትዮጵያን ጦርነት ጨምሮ ብዙ ውጣ ውረዶች ነበሩ፡፡ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የግብፅ መንግሥት አቅሙ በፈቀደ መጠን የሐሰት ፕሮፖጋንዳ ሲያሰራጭ ነበር፡፡ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ጫናዎች ሲደረጉ ነበር፡፡

እነዚህ ሁሉ የውጭና የውስጥ ጣጣዎች ሲደረጉ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግን እየተገነባ ነበር። ምንም እንኳን የነበረው የውስጥ የፖለቲካ ሁኔታ ያሳደረው ጫና አልነበረም ባይባልም የመላው ኢትዮጵያ የጋራ ጉዳይ የሆነው የታላቁ ኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግን እነሆ በቅብብሎሽ ቀጥሏል፡፡ ያለፈውን ትውልድ ከአሁኑ ትውልድ ጋር፤ የአሁኑን ትውልድ ከሚቀጥለው ትውልድ ጋር ሊያስተሳስር እነሆ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሷል፡፡

የዘንድሮውን የዓባይን ግድብ የመሠረት ድንጋይ የተጣለበትን ቀን መታሰቢያ ለየት የሚያደርገው የመጨረሻው ምዕራፍ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የህዳሴ ግድቡ የመሠረት ድንጋይ የተጣለበት ቀን የሚከበረው ለማስታወስ ብቻ እንጂ ግድቡ እዚህ ላይ ደርሷል፣ ይህን ያህል በመቶ ተጠናቋል በሚሉ አኃዛዊ መረጃዎች አይደለም፡፡ ከዚህ በኋላ የምናስታውሰው፤ የህዳሴ ግድቡ ግንባታ ከመጀመሩ እና ከመጠናቀቁ በፊት ኢትዮጵያ የነበራት የኤሌክትሪክ አቅርቦት ይህን ያህል ብቻ ነበር በሚል ታሪክን ለማስታወስ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን በዚህ ሥራቸው ሊኮሩ ይገባል። ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ልክ እንደ ዓድዋ ሁሉ የጋራ ኩራት፣ የጋራ ታሪክ፣ የጋራ ሀብት ነው።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ልክ እንደ ዓድዋ ሁሉ የይቻላል መንፈስን የሚያሳይ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ትርፍ የሚያስገኝ ነው፡፡ በራስ አቅም የመሥራትን፣ ጀምሮ የመጨረስን፣ ተደራድሮ የማሸነፍን አቅም የሚያሳይ ነው፡፡ እንደነኢንጂነር ስለሺ በቀለ ያሉ ጀግኖችን ልክ እንደነአክሊሉ ሀብተወልድ በዓለም አቀፍ የድርድር መድረክ ላይ በታሪክ የሚያስቀምጥ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ሆና ግዙፍ ፕሮጀክቶችን መሥራትና መፈጸም እንደምትችል ያስመሰከረ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆን በጋራ ጉዳዩ ላይ አንድ መሆኑን ያስመሰከረ ነው፡፡

በአጠቃላይ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ኢትዮጵያውያንን ያስተሳሰረ የታሪክ ገመድ ነውና የአብሮነትና የአሸናፊነት ተምሳሌት ሆኖ ትውልድን ያስተሳስራል!

# «የረመዷን ኢፍጣር» የኢትዮጵያውያን አብሮነት ማሳያ

**አማን ረሺድ**

ዘንድሮ የጊዜ አጋጣሚ ሆኖ ረመዷንና ዐቢይ ጾም ለአንድ ወር ያህል በተመሳሳይ ጊዜ ይጾማሉ። በእስልምናው እምነት ተከታዮች ዘንድ የረመዷን ወር ልዩ ቦታ ያለው ነው። በክርስትናም ቢሆን የዐቢይ ጾም የበረከት ሥራዎች የሚሠሩበት ጊዜ መሆኑ ዕሙን ነው። ታዲያ በእነዚህ የጾም ወራት ለተቸገሩ መርዳት፣ ጾመኞችን ጾም ማስፈታት ወይም ማስፈጠር የተለመደ ተግባር እየሆነ መጥቷል።

ጾመኞችን ከሚያስፈጥሩ ተቋማት መካከልም ባቡልኸይር በጎ አድራጎት ማኅበር አንዱ ነው። ወይዘሮ ሀናን ማሕሙድ የባቡልኸይር በጎ አድራጎት ማኅበር መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ናቸው። ወይዘሮ ሀናን ማሕሙድ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ የረመዷን ወር ያለእምነት ልዩነት አቅመ ደካማ ጾመኞችን ጾም ማስፈታት ወይም ማስፈጠር መቻል የኢትዮጵያውያን አብሮነት ማሳያ መሆኑን ይገልጻሉ። ለምስኪኖች አለኝታ መሆን የዱንያንም (የምድርን)ና የአኼራንም(ሰማያዊ) ደስታን ያጎናጽፋል ይላሉ።

በባቡልኸይር ቅጥር ግቢ ውስጥ አሁን ላይ በቀን አምስት ሺህ ያፈጥራሉ። ከ40 በላይ በጎ ፍቃደኛ የክርስትና እምነት ተከታዮች መጥተው በር ላይ ከማስተባበር ጀምሮ ቀድመው ሾርባ በመቅዳት፣ ቴምር በማከፋፈል እንዲሁም ወገኖቻቸውን ጾም ሲያስፈቱ ወይም ሲያስፈጥሩና አለኝታ መሆናቸውን ሲያሳዩ መመልከት ልዩ ስሜት እንደሚፈጥር ይገልጻሉ።

በተጨማሪም ጎረቤቶች ወደ ማኅበሩ መጥተው በፍቅር ሲያግዙና አቅመ ደካሞች በልተው ሲደሰቱ ማየት ከምንም በላይ ነው ባይ ናቸው። እንደ ሀገር ለአንድ ዓላማ ተባብሮ መቆም፣ መደጋገፍና መተሳሰብ ትልቅ ፋይዳ አለው የሚሉት ወይዘሮ ሀናን፤ ማኅበሩ ረመዷን ከመግባቱ በፊት በቀን ሰባት መቶ ሺህ ብር እንደሚያወጣ ያብራራሉ።

ዘንድሮ የረመዷን ወር በርካታ ዜጎች ወደ ማኅበሩ በመምጣታቸው አሁን ላይ የቀን ወጪ አንድ ሚሊዮን ብር መድረሱን ያስረዳሉ። ከእስልምና እምነት ተከታዮች በተጨማሪም አቅመ ደካማ የክርስትና እምነት ተከታዮች ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት እንደሚስተናገዱ ይናገራሉ። ይህም ማኅበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከር ሚናው የጎላ ነው።

በመቀጠልም እስከ ምሽት የእስልምና እምነት ተከታዮች ይስተናገዳሉ። የጾም መያዣ(ሱሁር)ና ጾም መፍቻ(ኢፍጣር) ቴምር፣ የገብስ ሾርባ፣ ዶናትና ስጋ ወጥ በማዘጋጀት አቅመ ደካሞች የማስፈጠር ተግባር እየተከናወነ መሆኑን ይገልጻሉ። ሕይወታቸውን ጎዳና ካዳረጉ ዜጎች ውጪ ያሉት ዜጎች የማፍጠሪያ ምግብ ወደ ቤት ይወስዳሉ። በረመዷን ወር ከወገኑ ጎን ቆሞ መገኘት ከሌሎች ግዜ ይለያል፤ ከዛም ባሻገር ተቸግረው ነገር ግን የሰው ዓይን ለማየት የሚፈሩ ዜጎችን ቤት ለቤት እንደሚደረስላቸው አንስተዋል።

ከአስር ዓመት በፊት ዩኒፎርም የለበሱ ተማሪዎች ከትምህርት ሰዓት ውጪ ከጎረምሶች ጋር እየተጋፉ ምግብ ሲመገቡ ማየታቸው ለማኅበሩ መመሥረት ምክንያት መሆኑን የሚናገሩት ወይዘሮ ሀናን፤ ተማሪዎቹ ለምን እንደወጡ ሲጠየቁ ተርበው እንደሆነ ገልጸውልኛል ይላሉ።

ከዚህም ባለፈ በርካታ አቅመ ደካማ ኢትዮጵያውያን የሚገጥማቸውን ችግር ለመቅረፍ ታስቦ መመሥረቱን ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ባለሀብቶች በሥራ እቅዳቸው ውስጥ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የበጎ አድራጎት ማኅበርን ለመጎብኘት ማቀድ ይኖርባቸዋል ይላሉ። ይህም ቀጣዩ ትውልድ መልካምነት ስላለው ዋጋ ትምህርት እንዲያገኙ እንደሚያደርግ ያስረዳሉ። በርካታ አረጋውያን እንዳይራቡ ለማድረግ የተከፈለው ዋጋ ከባድ ቢሆንም ለበጎነት የተከፈለ ስለሆነ ያኮራልም ያስደስታልም ሲሉ ይገልጻሉ።

ማኅበሩ ቋሚ ገቢ ባይኖረውም በልበ ቀና ኢትዮጵያውያን ድጋፍ በማሰባሰብ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ይናገራሉ። በመሆኑም ተቋማትና ግለሰቦች አቅማቸው በፈቀደ መጠን ለማኅበሩ ድጋፋቸውን እንዲያደርጉ መልዕክታቸውን አክለዋል።

# ከ100 ሺህ ሔክታር በላይ ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ምርትና ምርታማነት ሀገራዊ የሕልውና ጉዳይ መሆኑን አብራርተው፤ ምርታማነት ሲረጋገጥ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሱ በርካታ ችግሮችን መፍታት እንደሚቻል አስታውቀዋል።

ምርታማነት ጉዳይ ሀገራዊ አጀንዳ ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከድህነት አዙሪት ውስጥ በመውጣት ራሳችንን እንቻል ሲባል ምርትና ምርታማነትን በማረጋገጥ ጭምር ነው ብለዋል። ለዚህ ደግሞ የአፈርን ጤናማነት ማረጋገጥ እንደሚገባ ገልጸዋል።

እንደ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የአፈር ጤናማነት ካልተረጋገጠ ምርት ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ፤ እንደ ኖራ ባሉ የተለያዩ አማራጮች አሲዳማ አፈርን መከላከል ይገባል። ኖራ ርካሽና በቅርበት መገኘት የሚችል የግብርና ግብዓት በመሆኑ፤ ምርትን ለመጨመር የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ ኖራን ለአሲዳማ መሬት ማከሚያነት በመጠቀም ምርታማነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ይህን እውን ማድረግ የሚቻለው በመደማመጥ መንፈስ በመሥራት፤ የተሟላ ዕቅድ በማዘጋጀትና ሥራን በዲሲፕሊን በመፈጸም ሙያተኛና አርሶ አደሩ ጋር መድረሱን በማረጋገጥ ነው ብለዋል።

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ባለፉት ዓመታት በምርምር ተቋማት በግብርና ኤክስቴንሽን ሠርቶ ማሳያ እንዲሁም በተለያዩ ፕሮጀክቶች ሲከናወኑ በነበሩ ሥራዎች አሲዳማ አፈርን በግብርና ኖራ በማከም የሰብል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንደተቻለ አስታውቀዋል። የማስጀመሪያ የንቅናቄ መርሐግብር በግብርና ኖራ 100 ሺህ ሄክታር መሬት ለማከም ያለመ እንደሆነ ገልጸዋል።

የግብርና ኖራ የተጨመረባቸው ማሳዎች ከፍተኛ የምርት ጭማሪ ማሳየታቸውን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ለአብነትም ስንዴ 71 በመቶ፣ ገብስ መቶ በመቶ፣ በቆሎ 28 በመቶ፣ እንዲሁም ባቄላ 88 በመቶ ማሳደግ ተችሏል ነው ያሉት።

በኢትዮጵያ አሲዳማ አፈርን ለማከም የሚያስችል ከፍተኛ የኖራ ክምችት እንዳለ በማዕድን ሚኒስቴር በኩል መረጋገጡን ጠቁመዋል። የኖራን አቅርቦት ከማሻሻል አንጻር ክልሎች ካላቸው ውስን አቅም ጎን ለጎን የሲሚንቶ ፋብሪካዎች አምርተው ማቅረብ እንዲችሉ መግባባት ላይ እንደተደረሰም ጠቅሰዋል።

የግብርና ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያመላክተው፤ እየታረሰ ካለው የመሬት ሽፋን 43 በመቶ በአፈር አሲዳማነት የተጠቃ ነው። ከዚህ ውስጥ 28 በመቶ በጠንካራ አሲዳማነት የተጠቃ ሲሆን፣ ይህም በአጠቃላይ ከሚታረሰው መሬት ሦስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር ይሸፍናል።

# ለዓባይ ግድብ ግንባታ በዚህ ዓመት ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ዓመቱ ስምንት ወራት 931 ሚሊዮን 984 ሺህ 102 ብር ተሰብስቧል።

ገቢው የተሰበሰበው ከሀገር ውስጥ ቦንድ ግዢና ስጦታ፣ ከዲያስፖራ ቦንድ ግዢና ስጦታ፣ ከ8100 A፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት በገባ እና ከደረት ፒን ሽያጭ መሆኑን አስታውቀዋል።

የዓባይ ግድብ ከተጀመረበት መጋቢት 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ከሀገር ውስጥ ቦንድ ግዢና ስጦታ፣ ከዲያስፖራ ቦንድ ግዢና ስጦታ፣ ከ8100 A፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት በገባ እና ከደረት ፒን ሽያጭ ከ19 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን አስረድተዋል።

ግድቡን ለማጠናቀቅ የገቢ ማሰባሰብ ሂደቱ ተጠናክሮ መቀጠሉን ገልጸው፤ ከመጋቢት 18 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ "በኅብረት ችለናል" በሚል መሪ ቃል የታላቁ ህዳሴ ግድብ የቦንድ ሳምንት ይካሄዳል። በዚህም በቦንድ ሳምንቱ 100 ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ ታቅዷል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ሌሎችም ቦንድ የሚሸጡ የገንዘብ ተቋማት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ቦንድ ለመሸጥ ዝግጁ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

መላው ኢትዮጵያውያን በቦንድ ሳምንቱ ቦንድ በመግዛት ሊጠናቀቅ የደረሰው ግድብ ላይ አሻራቸውን እንዲያሳርፉ ጥሪ አቅርበዋል።

እንደ አቶ ኃይሉ ገለጻ፣ መላው ሕዝብ ለግድቡ ድጋፍ በማድረጉ ከግንባታ ምዕራፍ ወደ ውሃ ሙሌት እና ኃይል ማመንጨት ደረጃ ደርሷል። ግንባታው በጥቂት ወራት የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ከ42 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ በላይ ውሃ መያዙን ተናግረዋል።

አጠቃላይ የግድቡ የግንባታ ሂደት 95 በመቶ የደረሰ ሲሆን ቀሪ ሥራውን ለማጠናቀቅ ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ዋቄ በበኩላቸው፤ ቦንዶችን ከ25 ብር ጀምሮ በማሳተም ለኅብረተሰቡ የማሰራጨት ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።



# ለውጭ ገበያ ከቀረበ ቡና ከ716 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በ2016 በጀት ዓመት ስምንት ወራት ለውጭ ገበያ ከቀረበ የቡና ምርት 716 ነጥብ 35 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

የባለሥልጣኑ የሕዝብ ግንኙነትና የኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሣሕለማርያም ገብረመድኅን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበጀት ዓመቱ ስምንት ወራት 150 ሺህ 430 ነጥብ55 ቶን ቡና በመላክ 716 ነጥብ 35 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

በስምንት ወራት ውስጥ 211 ሺህ 370 ቶን ቡና ወደ ውጭ ሀገራት በመላክ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ እንደነበር አስታውሰው፤ የገቢ አፈጻጸሙ የእቅዱን 67 በመቶ መሆኑን አስረድተዋል።

በተጠቀሰው ጊዜ ወደ ውጭ የተላከው ቡና ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የሰባት ሺህ 228 ነጥብ 78 ቶን ጭማሪ እንዳለውም ጠቁመው፤ የዓለም የቡና ዋጋ አምና በተመሳሳይ ወቅት ላይ ከነበረው ጋር ሲነጻጸር በተከታታይ በመውረዱ ምክንያት አጠቃላይ የገቢ ዕቅዱን ማሳካት እንዳልተቻለ አንስተዋል፡፡

በየካቲት ወር ብቻ 19 ሺህ 245 ነጥብ 90 ቶን ቡና ወደ ውጭ በመላክ 88 ነጥብ 64 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱን አስታውሰው፤ አፈጻጸሙ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነጻጸር በመጠን ሁለት ሺህ 693 ነጥብ 17 ቶን፣ በገቢ ደግሞ የአምስት ነጥብ 38 ሚሊዮን ዶላር ጭማሪ እንዳለው አስታውቀዋል፡፡

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ ሳዑዲ ዓረቢያ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ አሜሪካ፣ ጀርመን፣ ጃፓን፣ ቤልጂየም፣ ቻይና፣ ሱዳን፣ ዩናይትድ ዓረብ ኤሜሬትስና ጣሊያን ዋነኛ የኢትዮጵያ ቡና መዳረሻ ሀገራት ናቸው።

ወደዋነኛ የኢትዮጵያ ቡና መዳረሻ ሀገራት የተላከው ምርት በአጠቃላዩ የቡና ወጪ ንግድ ጋር ሲነጻጸር በመጠን 80 በመቶ በገቢ ደግሞ 79 በመቶ የሚሆነውን እንደሚሸፍኑ አቶ ሣሕለማርያም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ቀዳሚዋ የምርቱ መዳረሻ ወደሆነችው ሳዑዲ ዓረቢያ ከተላከው 37 ሺህ 614 ነጥብ 41 ቶን ቡና 152 ነጥብ 36 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መገኘቱን አቶ ሣሕለማርያም አመላክተዋል።

12 ሺህ 583 ነጥብ 89 ቶን ቡና ደግሞ ወደ ደቡብ ኮሪያ በመላክ 72ነጥብ 84 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መገኘቱን ጠቁመው፤ ዘጠኝ ሺህ 438 ነጥብ 15 ቶን ቡና ደግሞ ወደአሜሪካ በመላክ 60 ነጥብ 27 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መገኘቱን አስረድተዋል።

የኢትዮጵያን የቡና ጥራትና ምርታማነት ማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ገቢውን ከፍ ለማድረግ የሚያስችል ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አመላክተዋል።

# ወቅታዊ

# «በዞናችን ያሉ አነስተኛ ከተሞች ሁሉ ከወንጪ ደንዲ ፕሮጀክት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንፈልጋለን»

**-አቶ ቶሎሳ ተረፈ**
**የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን አስተዳደር ጽህፈት ቤት ኃላፊ**

አስቴር ኤልያስ

**በኦሮሚያ ክልል የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ዞኑ በገበታ ለሀገር መርሃ ግብር ውስጥ ከተካተቱ እና በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት ተገንብተው ለምረቃ ከበቁ ፕሮጀክቶች አንዱ ነው፡፡**

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም አገልግሎት መስጠት ስለጀመረው ፕሮጀክት እና በዞኑ ስላሉ የልማት እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ስራዎች ከደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን አስተዳደር ጽህፈት ቤት ኃላፊ ከሆኑት ከአቶ ቶሎሳ ተረፈ ጋር ቆይታ አድርጓል፤ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- የዞኑን ማኅበረሰብን ተጠቃሚ በማድረግ በኩል የተሰራው የልማት እንቅስቃሴ እና የጸጥታ ሁኔታ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ቶሎሳ፡-** የአስተዳደሩ ጽህፈት ቤት ከአዲስ አበባ በ114 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ነው፡፡ በዞናችን 12 ወረዳ እና 316 ቀበሌዎች ይገኛሉ፡፡ እንዲያም ሆኖ በእነዚህ ሁሉ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ወደ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ማኅበረሰብ ይኖራል፡፡ በዚህ ውስጥ የተለያዩ የልማት ስራዎች፣ የጸጥታ ሁኔታ እና የመሰረተ ልማት ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው፡፡

በዚህ ጊዜ አንዳንዴ አነስተኛ የሆኑ የጸጥታ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ እሱን ለማስተካከል ደግሞ ከጸጥታው አካላት ጋር ሆነን የፖለቲካ አመራሩ አንድ ላይ ተቀናጅቶ የኅብረተሰቡን ሰላም እና ጸጥታ የማስከበር ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ ሁሉም ወረዳዎች ላይ በአሁኑ ሰዓት የልማት ስራዎች በስፋት እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ የተለያዩ ፕሮጀክቶችም እየተገነቡ ነው፡፡ ሌላ ቦታ እንደሚወራው የጸጥታ ችግር ሆኖብን ስራ ያቆምንበት ወረዳም ሆነ ቀበሌ በአሁኑ ወቅት የለም፡፡ ከዚህ የተነሳ የተለያዩ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡

በዘንድሮ ዓመት ብቻ ማኅበረሰቡ የሚጠቀምበት ወደ 235 የግንባታ ስራዎችን እየሰራን ነው፡፡ ይህንን ፕሮጀክት እየሰራን ያለነው ዘንድሮ ለመጨረስ ነው፡፡ በሌላ በኩል መንግስት የቀረጻቸው የተለያዩ ተነሳሽነቶች አሉ፤ ለምሳሌ አንዱ የበጋ ስንዴ ሲሆን፣ ይህን በስፋት እየሰራንበት ያለ ክንውን ነው፡፡

የበጋ ስንዴ በተለይ ወደ ሰበታ ሃዋስ እና ኢሉ አካባቢ የበጋ ስንዴ በስፋት በኩታ ገጠም ተዘርግቷል፡፡ እሱም በመልማት ላይ ነው። ገበታ ለአገር አካል የሆነው የወንጪ ደንዲ ፕሮጀክት የመጀመሪያው ምዕራፍ አልቆ በጠቅላይ ሚኒስትራችን ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡ ይህ ታላቅ ፕሮጀክት ተመርቆ ለስራ ክፍት መሆኑ የሰላሙንና የጸጥታውን መልካም መሆን ያመላክታል፡፡ ስራችንን አቅደን፣ ጀምረን እና ሰርተን መጨረስ ችለናል ማለት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከወራት በፊት የተመረቀው የወንጪ ደንዲ ፕሮጀክትን ለመጎብኘት በርካቶች ወደ ዞኑ መምጣታቸው አይቀሬ ነው፤ ይህን ፕሮጀክት ለማየት ለሚመጣው ቱሪስት ከመንገድ እና ከሌሎች መሰረተ ልማት አኳያ ምን ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለታል?**

**አቶ ቶሎሳ፡-** የወንጪ ደንዲ ገበታ ለአገር ፕሮጀክት የተሰራው በጠቅላይ ሚኒስትራችን ጠንሳሽነት ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት የመጀመሪያው ምዕራፍ ተጠናቅቋል፡፡ እዛ አካባቢ ያለው የውስጥ ለውስጥ መንገድ በሙሉ ተሰርቶ ያለቀ ነው፡፡ በዚህ በተሟሏ አሰራሩ ደግሞ ማኅበረሰቡ በጣም ደስተኛ ሆኗል፡፡

ከፕሮጀክቱ ጋር የሚገናኙ መስመሮች ለምሳሌ መብራት፣ ውሃ ሁሉ የተሰራለት ነው። ሌላው ቀርቶ ከስፍራው ለተነሱ 13 አርሶ አደሮች 150 ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገበት መኖሪያ ቤት ተገንብቶላቸዋል፡፡ መኖሪያ ቤት ብቻ ሳይሆን ሙሉ እቃ ጭምር ተሰጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህ እንደ ከዚህ በፊቱ ፕሮጀክት ሲሰራም ሆነ ኢንቨስትመንት ሲመጣ እና ሲሰራ የነበረው አርሶ አደሮችን እያፈናቀለ ነው፡፡ አሁን ግን በወንጪ ደንዲ ፕሮጀክት የተሰራው ቤተ መንግስት ማኅበረሰቡን አቅፎ ነው፡፡

የወንጪ ደንዲ ፕሮጀክት የሆነው ሎጅ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሆኖ የተሰራ ነው፡፡ የአካባቢውም አርሶ አደር፣ የተገነባለት ቤት ከእሱ ጋር የሚመጣጠን ነው፡፡ አርሶ አደሮቹ ራሳቸው ፕሮጀክቱን “የእኔ ነው” ብለው እንዲንከባከቡ የሚያግዝ ነው፡፡ በፕሮጀክቱ ውስጥ እንደ ዞናችን ወደ 839 ስራ አጦች ስራ እንዲያገኙ ተደርገዋል።

በተጨማሪ እንደዞን ለ36 ወጣቶች ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርገን ሳይክል ገዝተን አቅርበንላቸዋል፡፡ በተሰጣቸው ሳይክል በአሁኑ ወቅት የየራሳቸውን ስራ እየሰሩበት ይገኛል፡፡ እግረ መንገዳቸውን ቱሪስቶች ሲመጡ እያከራዩ ስለሆነ ማኅበረሰቡ በጣም ደስተኛ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም ፕሮጀክቱ የእሱ መሆኑን አውቋል፤ የፕሮጀክቱ መኖርም ተጠቃሚ እያደረገው ይገኛል፡፡

ነገር ግን ያለው ችግር የመንገድ ነው፡፡ እንዲህም ሲባል ችግሩ ከዚህ በፊት ተጀምሮ በነበረው በአምቦ ወሊሶ የአስፓልት መንገድ ነው። ከዚህ በፊት ከወሊሶ ወደ አምቦ ሲሰራ የነበረ ቢሆንም ከሁለትና ሶስት ዓመት በፊት ተቋርጦ ነበር፡፡ ፕሮጀክቱ የፌዴራል መንግስት ሲሆን፣ የሚያሰራው የፌዴራል መንግስት ነው፡፡ ይሁንና እሱ መንገድ እስካሁን አላለቀም፡፡

ከአምቦ እስከ ወንጪ ያለው መንገድ ግን አልቋል፡፡ ይኸኛው ስላላለቀ ኅብረተሰቡ ዘንድ ቅሬታ የፈጠረ ሲሆን፣ ቶሎ እንዲያልቅለትም ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም መንገዱ ከተፈጀመረ ወደ ስምንትና ዘጠነኛ ዓመት አስቆጥሯል፡፡ የወንጪ ደንዲ ፕሮጀክት በተመረቀበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆኑ የመከላከያ ሚኒስትሩ በተለይ የመከላከያ ሚኒስትሩ ዶክተር አብርሃም በላይ ፕሮጀክቱን የሚመሩት እርሳቸው ስለሆኑ ባለፈው ፕሮጀክቱ የወንጪ ደንዲ ፕሮጀክት አካል ሆኖ መንገዱ ቶሎ እንዲያልቅ አቅጣጫ አስቀምጠዋል። በዚህ አግባብ ሚኒስትሩ ጉዳዩን እየተከታተሉት ሲሆን፣ እኛም የኅብረተሰቡ ቅሬታ በነበረው ጉዳይ ላይ ምላሽ ስላገኘን በዚህ ደስተኞች ነን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- 236 ፕሮጀክቶች በመሰራት ላይ እንደሆኑ ተናግረዋል፤ ምን ምን አይነት ፕሮጀክቶች ናቸው?**

**አቶ ቶሎሳ፡-** ፕሮጀክቶቹ ባለፈው ዓመት ተጀምረው ባለመጠናቀቃቸው ምክንያት ለዘንድሮ የተላለፉ አሉ፤ ዘንድሮ ደግሞ ወደ አንድ መቶ ፕሮጀክቶች በእቅድ ተይዘው እየተተገበሩ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል መንገድ፣ ድልድይ፣ የውሃ ፕሮጀክቶችም የተካተቱበት ነው፡፡

ሌላው ቀርቶ የአስተዳደር ሕንጻም በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ የተካተተ ነው፡፡ ይህን ፕሮጀክት ስራ ለማስጀመር ጨረታ ሁሉ ወጥቶ ወደ ስራ



መግባት ችለናል፡፡ ይህ የአስተዳደር ሕንጻ ብቻ ባለ አምስት ወለል ሲሆን፣ ወደ 307 ሚሊዮን ያህል ብር ወጪ ተደርጎ የሚገነባ ፕሮጀክት ነው፡፡ ወረዳዎች ራሳቸው በማኅበረሰብ ተሳትፎ፣ በመንግስት በጀት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ልማታዊ ድርጅቶች የሚሰሩ ፕሮጀክቶች አሏቸው፡፡ ለአብነት ያህል ትምህርት ቤቶች፣ ውሃ፣ ድልድይ፣ መንገድ እና መሰል ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

በዚህ ዓመት እናጠናቅቃለን ብለን ያቀድነው 235ቱን ፕሮጀክቶች ሲሆን፣ አጠናቅቀንም ለኅብረተሰቡ አገልግሎት እንዲበቁ ለማድረግ እየሰራን ነው፡፡ በእስካሁኑ ሒደት 26ቱን ፕሮጀክቶች ጨርሰናል፡፡ ይሁንና ፕሮጀክቶቹ የሚመሩት በመርሃግብር እንደመሆናቸው ገና አልተመረቁም፤ ነገር ግን በቅርቡ ለምረቃ የሚበቁ ይሆናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የወንጪ ደንዲ የአገር ፕሮጀክትም ጭምር ነው፤ ወደዚህ ስፍራ ቱሪስቶች በስፋት ይመጡ ዘንድ በእናንተ በኩል ምን አይነት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ተዘጋጃችሁ? እንደ ዞን ከፕሮጀክቱስ ምን ትጠብቃላችሁ?**

**አቶ ቶሉሳ፡-** በዚህ ፕሮጀክት የወሊሶ ከተማ ብቻ ሳይሆን በዞናችን ውስጥ ያሉ አነስተኛ ከተሞች ሁሉ ከወንጪ ደንዲ ፕሮጀክት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንፈልጋለን፡፡ እየሰራን የምንገኘው ለዚያም ነው፡፡ ልክ ከአዲስ አበባ ሲወጣ ከሰበታ ቀጥሎ ተፍኪ በዞናችን ውስጥ የምትገኝ ከተማ ስትሆን፣ ከዚያ እዚህ ወሊሶ ድረስ እስኪመጣ እና ከወሊሶ አልፎ ደግሞ ጪቱ እስከ ሀሮ ያሉ ከተሞች መስመር ላይ ናቸው፡፡ በዚያኛው በኩልም እስከ አምቦ ድረስ ያሉ ከተሞች መስመር ላይ ናቸው፡፡

ስለዚህ የተነሳው ጥያቄ አግባብነት ያለው ነው፤ ሆቴሎቻችን ለሚመጡ ቱሪስቶች ምቹ ይሆኑ ዘንድ እና ባለሀብቶቻችን እንዲነቃቁ ከአንዴም ሁለቴ የባለሀብቶች ፎረም ፈጥረን ከወሊሶ ከተማ አስተዳደር ጋር በመሆን ስብሰባ አካሂደናል። በተለይ በዞናችን የሚገኘው የምግብም ሆነ የባህል፣ የምግብ እና የአልባሳት በጥቅሉ ዞኑን በአግባቡ የሚገልጹ ነገሮችን እንዴት አድርገን መጠቀም እንዳለብን ወይይት አድርገናል፡፡

ከተሞች ብቻ ሳይሆኑ የትኛውም ቱሪስት ወደዞናችን ሲመጣ በየአካባቢው እና በየደረሰበት እያረፈ እየተዝናና እንዲሁም አርሶ አደሩ ዘንድም እየቆየ መሄድ የሚያስችለውን ሁኔታ ለመፍጠር ነው እየሰራን ያለነው፡፡ ስለሆነም አርሶ አደሮቻችን ባላቸው አቅም ቱሪስቶች ወደመንደራቸው ሲመጡ ሁኔታዎችን ምቹ እንዲያደርጉ በስፋት ተወያይተናል፤ የማነቃቂያ ምክክርም አድርገናል። ስለሆነም የእኛ ነው፤ እንደ አገር የተሰራ ፕሮጀክት ቢሆንም በደንብ ተጠቃሚ መሆን የሚያስችለን እኛን ነው ብለን እናምናለን፡፡

በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ 839 ስራ አጦች የስራ እድል የፈጠረ ፕሮጀክት ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፤ ገና በዚህ ፕሮጀክት ከዚያም በላይ እንጠቀምበታለን፡፡ ፕሮጀክቱ ግዙፍ እና የአገርም የእኛም ሀብት እንደመሆኑ ለመጠቀም ዝግጁዎች ነን፡፡

ለምሳሌ የስራ እድሉን በተመለከተ እንደ ዞናችን ያቀድነው በዚህ በ2016 ዓመት 73 ሺ 964 ስራ አጦችን ወደስራ እናስገባለን ብለን ነው።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ወቅታዊ

ከገጽ 7 የዞረ

## «በዞናችን ያሉ አነስተኛ ከተሞች...



**የትምህርትን ጥራት ለማስጠበቅ በሚደረገው ሒደት የሚጎድሉ የትምህርት ግብዓቶች ይኖራሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የመማሪያ መጽሐፍት ሲሆን፣ መንግስት በቶሎ የመማሪያ መጽሐፍትን ማድረስ ይጠበቅበታል**

እስካሁን ካቀድነው ውስጥ ወደስራ ያስገባነው ስራ አጥ 44 ሺ 535 ሲሆን፣ ይህ እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ያለው አኃዝ ነው፡፡ በዚህም ከእቅዳችን ያሳካነው 60 ነጥብ ሁለት በመቶ ነው፡፡ ይህ ማለት የቋሚ ሰራተኞችን ብቻ የሚመለከት አኃዝ ነው፡፡ ጊዚያዊ የሆኑትን በሪፖርት መልክ አንይዝም፤ ጊዚያዊ የሆኑ ሰራተኞች በብዛት የተቀጠሩ ቢሆንም፤ የተወሰነ ጊዜ ሰርቶ ወዲያው ደግሞ ላይኖር ስለሚችል ቁጥራቸው የሚያካትተው ቋሚ ሰራተኞች ብቻ ነው፡፡ ክልልም ቢሆን የሚወስደው ሪፖርት የቋሚ ሰራተኞችን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት የትምህርት ቤቶች ደረጃ ማሻሻል ላይ እንዲሰራ አቅጣጫ ማስቀመጡ ይታወቃል፣ በዚህ ዞን ከትምህርት ቤት ተደራሽነትና ከደረጃ ማሻሻል ጋር ተያይዞ ምን እየተሰራ ስራ?**

**አቶ ቶሌሳ፡-** በዞናችን ደረጃ መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ በትምህርት ቤት ላይ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ናቸው፡፡ በተለይም በዞናችን ከመዋዕለ ሕጻናት ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያሉት ከ450 በላይ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ከዚያ ውስጥ 309 ሺ እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ ብቻ ሳይሆን የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ መንግስትም ትኩረት ሰጥቶት የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሻሻል ስራ እንዲሁም እንደ ኦሮሚያ ክልል ደግሞ ከታች ጀምረን በትውልድ ላይ ካልሰራን አሁን ያለው ትውልድ ትንሽ የትምህርት ጥራት ላይ ችግር እያሳየ በመሆኑ በክልላችን ፕሬዚዳንት አቅጣጫ ተቀምጦ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡

ከዚህ ውስጥ ለአብነት "ቡዑራ ቦሮ" የሚባለውን መርሃ ግብር መተግበር ጀምረናል። በከተሞች አካባቢ በየትምህርት ቤት ውስጥ መዋዕለ ሕጻናት አለ፡፡ የአርሶ አደሩ ልጆች ግን ይህን እድል አያገኙም፡፡ ሰባት ዓመት ሲሞላቸው ቀጥታ ምንም ማንበብ እና መጻፍ ሳይሞክሩ አንደኛ ክፍል ለመግባት ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይመጣሉ፡፡ በከተማ ውስጥ ያሉ ሕጻናት ደግሞ ገና ከሶስት ዓመታቸው ጀምሮ በመዋዕለ ሕጻናት ውስጥ ከኬጂ ጀምሮ ያለውን ይማራሉ፡፡ በዚህም ውስጥ ፊደል መቁጠሩን ጨርሰው እና ለይተው አንደኛ ክፍል ለመግባት ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይመጣሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ፈተና የሚሆነው ነገር የአርሶ አደሩን ልጆች እና የከተማን ልጆች አንደኛ ክፍል እኩል አስቀምጦ ማስተማሩ ነው፡፡

ትምህርት ቤት ገብቶ የማያውቅ እና ሶስት ዓመት ሙሉ ስለትምህርት ሁኔታ የሚያውቅ ተማሪ ጋር የአርሶ አደሩን ልጅ ማስቀመጥ ሞራል መንካት በመሆኑ በትምህርታቸውም ወደኋላ እንዲቀሩ የሚያደርግ ነው፡፡ በእርግጥ በርከት ያለው ቁጥር የሚኖረው በገጠሩ ክፍል ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን ችግር ለመፍታት "ቡዑራ ቦሩ" የሚባል እንደ ኦሮሚያ ክልል የክልላችን ፕሬዚዳንት አቅጣጫ እንዳስቀመጡት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ መዋዕለ ሕጻናት ራሱን ችሎ ተገንብቶ እንዲከፈት እና በዞናችን ያሉ ሶስት ዓመት የሞላቸው ሕጻናት ልክ እንደከተማ ሕጻናት ሁሉ ወደመዋዕለ ሕጻናት ገብተው የመማር እድሉን እንዲያገኙ ብዙ ስራዎች እየተሰሩ ናቸው፡፡

ባለፈው ዓመት ብቻ የአርሶ አደሩን ልጆች ተጠቃሚ የሚያደርግ ወደ 221 መዋዕለ ሕጻናት በእያንዳንዱ ቀበሌ መስራት ችለናል፡፡ ዘንድሮ የያዝነው እቅድ ደግሞ ቀሪዎቹን 94 መዋዕለ ሕጻናት እንሰራለን የሚል ነው፡፡ እስካሁን 85ቱን አጠናቅቀን ስራ አስጀምረናል፡፡ በአሁኑ ወቅት ከ400 በላይ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መዋዕለ ሕጻናት ተሰርተው አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡

ልክ ከ"ቡዑራ ቦሮ" የሚወጡ ተማሪዎች ወደ አንደኛ ክፍል እንደሚገቡ ሁሉ፤ ከዚያ የሚወጡ የተመረጡ እና ጎበዝ የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ብቃታቸው ታይቶ የስምንተኛ ክፍል ትምህርታቸውን በጥሩ ሁኔታ ሲጨርሱ ከዘጠኝ እስከ 12ኛ ክፍል "ኢፋ ቦሮ" በሚባል ትምህርት ቤት እንዲማሩ በማድረግ ላይ ነን፡፡

"ኢፋ ቦሮ" በሚል በዞናችን ደረጃ የተገነቡ ሶስት ትምህርት ቤቶች አሉን፡፡ አንደኛው ሃሮ ወንጪ (የወንጪ ሐይቅ) ላይ ማለትም ፕሮጀክቱ የሚሰራበት ቦታ አንዱ ሲሆን፣ ሶዶ ዳጬ ላይም እየሰራን ነው፡፡ ምንም እንኳ የትምህርትን ጥራት በአንድ ጀምበር ማስተካከል የሚቻል ባይሆንም በዚህ አካሄድ ጥራቱን ለማስጠበቅ የበኩላችንን እየተወጣን እንገኛለን፡፡

"ኢፋ ቦሮ" በሚል የተገነቡ ሶስት ትምህርት ቤቶች ቢሆኑም ይሁንና በቂ ናቸው ብለን አንወስድም፡፡ በትምህርት ቤቱ የመማር እድል የሚደርሳቸው በትምህርታቸው ጎበዝ እንደሆኑት ሁሉ በ"ኢፋ ቦሩ" ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራንም ራሳቸው ወደዚያ ትምህርት ቤት ገብተው ማስተማር የሚችሉት ተፈትነው ካለፉ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም በተማሪዎች ብቻ ሳይሆን በመምህራንም በኩል የተመረጡ የሚገቡበት ትምህርት ቤት ነው ማለት ይቻላል፡፡

መደበኛ በምንላቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ የመማሪያ መጽሐፍቱ፣ ቤተ መጻሕፍቱ፣ ቤተ ሙከራውም ሆነ ሌላ ሌላውም ሲታይ "ኢፋ ቦሩ" ትምህርት ቤት የተሻለ ነው፡፡ መንግስት እነዚህ ትምህርት ቤቶች ላይ ትኩረት አድርጎ ስለሰራ ተመራጭም ነው፡፡ ይሁንና በእነዚህ በዞናችን ውስጥ በሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች መማር የሚያስችላቸው ተማሪዎች ብቁ የሆኑ እና ጉብዝናቸውን ከመጡበት ትምህርት ቤት ያረጋገጡ ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ ነጥባቸው ታይቶ መግባት ይችላሉ፡፡ በ"ኢፋ ቦሮ" በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እስከ 340 የሚሆኑ ተማሪዎች በመማር ላይ ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቱ የጀመረው ዘንድሮ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት እየተማሩ ያሉት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

የትምህርትን ጥራት ለማስጠበቅ በሚደረገው ሒደት የሚጎድሉ የትምህርት ግብዓቶች ይኖራሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የመማሪያ መጽሐፍት ሲሆን፣ መንግስት በቶሎ የመማሪያ መጽሐፍትን ማድረስ ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም የመማሪያ መጽሐፍት ተቀይሯል፡፡ እዚህ ግን አልደረሰም። ስለዚህም የአሁን እና የዘንድሮ እየተባለ ከሚሰራ አዳዲሱን መጽሐፍት በተቻለ መጠን ወደተማሪዎች ማድረስ ያስፈልጋል፡፡ ግብዓቱ በዚያ መንገድ ሲስተካከል እኛ ደግሞ መሰረቱን እያስተካከልን እንጓዛለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዞኑ የመልካም አስተ ዳደር ችግሮችን ለመፍታት እና የአገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ቶሌሳ፡-** የመልካም አስተዳደር ችግርን በተመለከተ እንደ መንግስትም ተለይተው የተቀመጡ አሉ፡፡ እኛም እንደዞናችን የመንግስት አቅጣጫን ተቀብለንና አቅደን ከዞን አመራሩ ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ማኅበረሰቡን የፖለቲካ አመራሩ፣ የቢሮ ኃላፊዎች በሳምንት ሶስት ቀን ማለትም ሰኞ፣ ረቡዕ እና ዓርብ ሌሎች ስብሰባዎችን ትተው በቢሯቸው ሆነው ማኅበረሰቡን እንዲያገለግሉ ማድረግ ችለናል። እንዳጋጣሚ ሆኖ አመራሩ በተለያየ ምክንያት የማይገኝ ከሆነ ሌላ ሰው በመወከል የባለጉዳዩን ቅሬታም ሆነ ጥያቄ እንዲስተናገድ ይደረጋል። ይህም ማኅበረሰቡ እንዳይጉላላ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ብዙ ስራዎች እየተሰሩ ነው። ወደ ወረዳም ወርደው ስለሚደግፉ የወረዳው ደግሞ ወደገጠር ድረስ ወርዶ ማኅበረሰቡን ስለሚያስተባብር በዚያን ጊዜ እንዲሁ ክፍተት እንዳይፈጠር በውክልና እንዲያሰሩ ይደረጋል፡፡ በዚህን ጊዜ ማኅበረሰቡ የሚያነሳቸውን ችግሮች በማዳመጥ በአግባቡ ምላሽ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

በዚህ ስራችንም ቀደም ሲል ከነበረው በተሻለ ለውጥ ማምጣት ችለናል፡፡ ሰው ባገኘው እና ባቀደው መሰረት የማይሄድ ከሆነ ማኅበረሰቡ መጥቶ ስለሚንገላታ እንደዚያ እንዳይሆን ቀናትን መድበን በማስተናገድ እና ችግራቸውንም እያየን መፍታት ብሎም ምላሽ መስጠት ላይ እየሰራን ነው፡፡

ከዚህ ሌላ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ይበዛባቸዋል ተብለው የተለዩት መስሪያ ቤቶችንም ለይተን በውስጡ ያሉ ችግሮች ምን እንደሆኑ እና እንዴት ነው መፈታት ያለባቸው በሚልም ከየመስሪያ ቤቶቹ ጋር አቅደን እየሰራን ነው። ለአብነት ያህል የመሬት አስተዳደርን መውሰድ ይቻላል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በየአነስተኛ ከተማ ያሉ ማዘጋጃ ቤቶች፣ መንገድ ትራንስፖርት አካባቢ እንዲሁም ማኅበረሰቡ በስፋት የሚገለገልባቸው ጽ/ቤቶች ላይ በብዙ አቅደን ስራ እየሰራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት እንደ አገር የተያዘ መርሃ ግብር አገራዊ የምክክር ኮሚሽን እያስኬደው ያለ ጉዳይ ነው፤ ከዚህ አኳያ ሒደቱ የተሳለጠ ይሆን ዘንድ በዞናችሁ የሚደረገው ድጋፍ ምን ይመስላል?**

**አቶ ቶሌሳ፡-** የአገራዊ ኮሚሽን ምክክሩ ዘንድሮ ወደስራ እየገባ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ዞናችን የምክክር መድረኩን በተመለከተ ድጋፉ ሙሉ ነው፡፡ በዚያ ውይይት ላይ አጀንዳ ለመለየት እና ለመሳተፍ የሚችሉትን እንደ ዞናችን በተጠየቅነው መሰረት ለይተን መስጠት ችለናል፡፡

እንደ አገር ዛሬ ላይ የተፈጠረ የመሰለን ችግር ዛሬ የተፈጠረ ሳይሆን ቀደም ሲል እየተደራረበ የመጣ ችግር ነው፡፡ እነዚያ ተደራርበው ዛሬ ላይ የደረሱ ችግሮች ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ተፈትተው ሰላም ይፈጠራል ተብሎ ይታሰባል። ከኮሚሽኑም የምንጠብቀው ተስፋ ብዙ ነው። ደግሞም የነበሩ ችግሮች እንደሚፈቱም ተስፋ አለን፡፡

ስለሆነም እንደ ዞናችን ከዚህ በፊት በመጀመሪያ ጊዜ የተመረጡ ሰዎች በኮሚሽኑ ጥያቄ መሰረት ሔደው ከኮሚሽኑ ጋር ምክክር አድርገው መጥተዋል፡፡ እናም በወቅቱ በሙሉ ድጋፍ፤ ያንን ማድረግ ችለናል፡፡ እንዲሁ በተመሳሳይ ለሁለተኛ ዙር ከአንድ ወር በፊት አዳማ ላይ ተመካክረው ተመልሰዋል፡፡ ውይይቱ ሲካሄድ የነበረውም በየክላስተሩ ነው፡፡ ከዚህ በኋላም ኮሚሽኑ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ መሰረት ሙሉ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁዎች ነን፡፡ ምክንያቱም ከዚህ የምክክር መድረክ የምናገኘው ጥቅም እንዳለ ስለምናውቅ የበኩላችንን ለማድረግ ዝግጁዎች ነን፡፡ ጉዳዩም የእኛው ነው ብለን በመከታተል ላይም እንገኛለን፡፡ ስለዚህም ሙሉ ድጋፍ እያደረግን ነው፡፡ ውጤት እንደሚመጣም ተስፋ አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ቶሌሳ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## በገበያ ትስስር የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት የማሳደግ ጥረት

አንተነህ ቸሬ



የኢንዱስትሪ ፓርኮች (Industrial Parks) ልማት የኢትዮጵያን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን እውን ለማድረግ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል ተብለው ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል አንዱ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የመሳብ፣ የሥራ እድል ፈጠራን የማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን የማድረግ ዋና ዋና መሰረታዊ ተልዕኮዎች አሏቸው። ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል ስራ በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል፡፡

በተለይም የግብርና ውጤቶችን እሴት በመጨመር በብዛትና በጥራት ተወዳዳሪ የማድረግ አቅም እንዳላቸው የታመነባቸው የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ((Integrated Agro-Industry Parks)፣ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ያሳካሉ ከተባሉ የኢንዱስትሪ ፓርክ ዘርፎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለአርሶ አደሮች የግብይት ሰንሰለቱን ቀላል በማድረግ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የገበያ ትስስር ይፈጥራሉ፡፡ ባለሀብቶች የግብርና ግብዓቶችን ከአርሶ አደሮች እንዲቀበሉ በማድረግ አርሶ አደሮች የልፋታቸውን ያህል እንዲጠቀሙ አወንታዊ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ፡፡

መንግሥት አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለመገንባት እስካሁን ድረስ ከ30 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ማድረጉንና ይህ ወጪ ባለሀብቶች በፓርኮቹ ውስጥ ገብተው በምርት ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ለሚያስችሉ ስራዎች የዋለ እንደሆነ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የሲዳማ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተገነቡና የመሰረተ ልማት አገልግሎት ተሟልቶላቸው ወደ ስራ ከገቡት የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል አንዱ የሆነውና በሀገሪቱ ከሚገኙ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል ቀድሞ ወደ ስራ የገባው የይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ለአርሶ አደሮች የገበያ ትስስር እድል በመፍጠር ለአግሮ-ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች፣ እድገት ምቹ ሁኔታ ከሚፈጥሩ እድሎችና ግብዓቶች መካከል አንዱ ሆኗል፡፡

በሲዳማ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን፣ ፈቃድና መረጃ ዳይሬክተር አቶ ታሪኩ ሮባ እንደሚገልፁት፣ በአሁኑ ወቅት ከ25 በላይ አልሚዎች ከሲዳማ ክልል ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር ውል ፈፅመው ወደ ፓርኩ ገብተው ለማምረት በተለያየ የትግበራ/ስራ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ኩባንያዎቹ በመደበኛ ምርት፣ በሙከራ ምርት እንዲሁም በማሽን ተከላ ላይ ይገኛሉ፡፡ አምራች ድርጅቶቹ በአቮካዶ፣ በማንጎ፣ በእንጆሪ፣ በቡና፣ በማር፣ በወተት፣ በስጋ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በአኩሪ አተርና በሌሎች ምርቶች ማቀነባበር ተግባራት ላይ የተሰማሩ ናቸው፡፡

በሙሉ አቅማቸው እየሰሩ ከሚገኙት ኩባንያዎች፤ የአቮካዶ ዘይት በማቀነባበር ለውጭ ገበያ፣ ወተት እና የተለያዩ የፍራፍሬ ጭማቂዎችን በማቀነባበር ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲሁም የማር ምርትን ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡት አምራቾች ናቸው፡፡ ምርቶቹን ለሀገር ውስጥ ገበያ ከማቅረብ በተጨማሪ ወደ ውጭ ለመላክ በተደረገ ጥረት አበረታች ውጤት ተገኝቷል፡፡

የይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ለምርት የሚያገለግለውን የጥሬ እቃ አቅርቦቱን የሚያገኘው ከአካባቢው ማኅበረሰብ ነው፡፡ የአካባቢው አርሶ አደሮች የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸዋል፡፡ ፓርኩ ስድስት (በሲዳማ ክልል ሦስት እና በጌዴኦ ዞን ሦስት) የገጠር ሽግግር ማዕከላት አሉት፡፡ ከእነዚህም መካከል አርሶ አደሮች በበንሳ ዳዬ፣ አለታ ወንዶ እና ሞሮቾ አካባቢዎች በሚገኙት ማዕከላት እና በኅብረት ስራ ማኅበራት በኩል የአቮካዶ፣ የማር፣ የወተት፣ የቡናና ሌሎች የግብርና ምርቶችን በፓርኩ ውስጥ ለተሰማሩ አልሚዎች እያቀረቡ ነው፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የማር እንዲሁም የወተት ምርት የሚያቀርቡ ማኅበራት ግብዓቶችን የሚሰበስቡት በገጠር የሽግግር ማዕከላቱ በኩል ነው፡፡ ፓርኩ ግብአቶችን በማቅረብ የገበያ ትስስርና የገቢ ምንጭ ከፈጠረላቸው አርሶ አደሮች በተጨማሪ በየዓመቱ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ፈጥሯል፡፡ ይህ ተግባር የሥራ እድል የመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሬ ወጪን የማስቀረትና ገቢ ምርቶችን የመተካት ድርብርብ ዓላማዎች አሉት፡፡

ከዚህ ቀደም አርሶ አደሮች አቮካዶ ለነጋዴዎች ሲሸጡ በዝቅተኛ ዋጋ ያቀርቡ እንደነበር አቶ ታሪኩ አስታውሰው፣ ግብዓቱን በቀጥታ ለፓርኩ አምራቾች ሲያቀርቡ ግን የተሻለ ገቢ ማግኘት እንደቻሉ ያስረዳሉ፡፡ ከሦስት ዓመታት በፊት ትልቅ ገበያ ያልነበረው የአቮካዶ ምርት በአሁኑ ወቅት ደረጃ ወጥቶለት አርሶ አደሩ ምርት በስፋት እያቀረበ፣ ገቢ እያገኘና አዳዲስ ዝርያዎችን እያለማ ነው፡፡ ፓርኩ አርሶ አደሩ ጥሬ እቃን በብዛትና በጥራት እንዲያቀርብ እድል እየፈጠረ ነው፡፡ ይህም የግብርና ምርታማነት እንዲጨምርና የአርሶ አደሩ ሕይወት እንዲሻሻል እያደረገ ነው፡፡

አርሶ አደሮች በፓርኩ ውስጥ ለተሰማሩ አምራቾች ግብዓት አቅርበው ተጠቃሚ ከመሆናቸው ባሻገር የአቅም ግንባታ ድጋፎችንም ያገኛሉ፡፡ በፓርኩ ውስጥ የተሰማሩ ባለሃብቶች ግብዓቶችን ከየአካባቢው ሲሰበስቡ ለአርሶ አደሮች ስልጠናዎችን ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ግብዓቶች በጥራት እንዲቀርቡና ምርታማነት እንዲጨምር እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ስለሆነም ፓርኩ የግብዓቶችን ጥራት በማሻሻል ምርታማነት እንዲጨምር ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በፓርኩ ዙሪያ ያሉ አካባቢዎች ለፓርኩ ግብዓት የማቅረብ አቅም ያላቸው በመሆኑ፣ በፓርኩ ውስጥ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ተግባራት ለአርሶ አደሮች የገበያ ትስስርም ሆነ የስራ እድል በመፍጠር የአካባቢውን ኅብረተሰብ ተጠቃሚነት የሚያሳድጉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ባለሀብቶች ወደ ይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው እንዲያለሙ የሚከናወኑት የፕሮሞሽን፣ የአገልግሎት አሰጣጥና የክትትል ተግባራት በልዩ ትኩረት የሚከናወኑ ይሆናሉ፡፡

በሚያዝያ ወር 2013 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተመረቀው በኦሮሚያ ክልል፣ ምስራቅ ሸዋ ዞን፣ አዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ፣ ከባቱ ከተማ በ16 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው የ«ቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ» የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የወተት፣ የማር፣ የስጋና የእንቁላል ምርቶችን የሚያቀነባብሩ አምራቾች የሚሰማሩበት የኢንዱስትሪ ፓርክ ነው፡፡

በኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ጌታሁን አዱኛ እንደሚናገሩት፣ የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ባለሀብቶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ባከናወናቸው ተግባራት ፈቃድ የወሰዱ 29 ኩባንያዎች ወደ ፓርኩ ገብተው በግብርና ምርቶች ማቀነባበር ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችሏቸውን የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ባለሀብቶቹ የሚሰማሩባቸው የአግሮ-ፕሮሰሲንግ (ግብርና ማቀነባበር) ዘርፎች የማርና ሰም፣ የምግብ ዘይት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ (ቲማቲም፣ ድንች፣ ጭማቂ… )፣ የቡና፣ የአቮካዶ ዘይት፣ የስጋ፣ የወተት፣ የእንስሳት መኖ፣ የፓስታና ማካሮኒ፣ የሕፃናት ምግቦች ማምረትና ማቀነባበር ስራዎች ናቸው፡፡

ወደ ፓርኩ ከገቡት ኩባንያዎች መካከል «ሸካ ኖርዲክ» ኩባንያ በማርና ሰም እንዲሁም «ቲኬ ግሩፕ» (TK Group) በምግብ ዘይት ማቀነባበርና ማምረት ላይ ተሰማርተው የሙከራ ምርት ጀምረዋል፡፡ «ቲኬ ግሩፕ» የተባለው ኩባንያ ሰባት የምርት ዓይነቶችን ለማምረትና ለማቀነባበር ከኦሮሚያ ክልል ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር ስምምነት የፈፀመ ድርጅት ነው፡፡

ሌሎቹ ድርጅቶች ደግሞ መሬት ተረክበው የባንክ ብድር ለማግኘት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶቹም የባንክ ብድር ተፈቅዶላቸው ማሽን ማስገባት ጀምረዋል፡፡ ለአብነት ያህል መንግሥት ለናሙና ወደገነባቸው ስድስት ሼዶች ውስጥ ከገቡት አምራቾች መካከል ሁለቱ የብድር ፈቃድ ሂደቶችን አጠናቅቀው ማሽኖችን እያስገቡ ይገኛሉ። ወደ ፓርኩ ገብተው ስራ ለመጀመር ፈቃድ ከወሰዱት ባለሃብቶች መካከል አብዛኞቹ የሃገር ውስጥ ባለሃብቶች መሆናቸውንም አቶ ጌታሁን ይናገራሉ፡፡

እንደ አቶ ጌታሁን ገለፃ፣ ከፓርኩ ጋር ትስስር ያላቸውና ግንባታቸው የተጠናቀቀ ስድስት የገጠር ሽግግር ማዕከላት ያሉ ሲሆን፤ የማዕከላቱ ዋና ተግባር የአርሶ አደሩን ምርት በጥራትና በብዛት ሰብስቦ ለፓርኩ አምራቾች ማቅረብ ነው። ወደ ፓርኩ የሚገቡት ባለሀብቶች ከሽግግር ማዕከላቱ ጋር በሚፈጥሩት ትስስር አርሶ አደሩን ጨምሮ የአካባቢው ኅብረተሰብ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ በሻሸመኔ፣ መቂ፣ ዶዶላ፣ ባሌ ሮቤ፣ ኢተያ እና አለንጪቲ የሚገኙት እነዚህ ማዕከላት ግንባታቸው ተጠናቆ መሰረተ ልማቶችን (ውሃ፣ መብራት፣ መንገድ…) የማሟላት ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ የሁሉንም ማዕከላት ግንባታና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ስራዎች በፍጥነት ለማጠናቀቅ ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ የግብርና ውጤቶችን በማቀነባበር ላይ አተኩሮ የሚሰራ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህ ሂደት ለፓርኩ ምርቶች የግብርና ግብዓቶችን የሚያቀርቡ በግብርና ስራ ላይ የተሰማሩ የአካባቢው ነዋሪዎች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ፓርኩ በማር፣ በስጋ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በዘይትና በጥራጥሬ ማቀነባበር የሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚገቡበት በመሆኑ አርሶ አደሮች ለአምራቾቹ ግብዓት በማቅረብ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

የፓርኩ ግንባታ ብዙ የሰው ኃይልና ግብዓት የሚፈልግ ስለነበር፣ በፓርኩ ግንባታ ወቅት በርካታ የአካባቢው ኅብረተሰብ ተጠቃሚ እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ ጌታሁን፣ አምራቾች ስራ ሲጀምሩ የአካባቢው አርሶ አደሮች ለፓርኩ የግብርና ግብዓቶችን በማቅረብ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ያስረዳሉ፡፡ «ፓርኩ በጥናት ላይ ተመስርቶ ሲገነባ ያስገኛል ተብሎ የታሰበው ዋና ጥቅም የአርሶ አደሩን ምርት በጥራትን በመጠን በመጨመር እንዲሁም የገበያ እድል በመፍጠር አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡ አሁን ባለሃብቶች ገና ወደ ፓርኩ ለመግባት በዝግጅት ላይ በመሆናቸው ስለአርሶ አደሩ ሰፊ ተጠቃሚነት ለመናገር ጊዜው ገና ነው፡፡ በምግብ ዘይት ምርት የሙከራ ምርት የጀመረው «ቲኬ ግሩፕ» ዘይት የሚያመርተው ከአኩሪ አተር ስለሆነ ግብዓቱን (አኩሪ አተር) እየሰበሰበ ይገኛል፤ አኩሪ አተር አምራች አርሶ አደሮች ተጠቃሚ እየሆኑ ነው» ይላሉ፡፡

በተጨማሪም «የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ የግብርውን ዘርፍ ለማሳደግ ታልሞ የተገነባ በመሆኑ የሚጠቀመው ግብዓት የሀገር ውስጥ የግብርና ምርቶችን ነው፡፡ በፓርኩ አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ አርሶ አደር ነው። የፓርኩ አምራቾች የሚጠቀሙት ጥሬ እቃ የአካባቢውን የግብርና ምርት ነው፡፡ አርሶ አደሩ ግብርናውን በማዘመንና አምራችነቱን በመጨመር ለምግብና ለገበያ ከሚያውለው ምርት በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን ትርፍ ምርት እንዲያመርት እየተሰራ ነው፡፡ በቀጣይ አምራቾች በማር፣ በስጋ፣ በዶሮ፣ በወተት፣ በጥራጥሬ፣ በዘይትና በሌሎች ዘርፎች ወደ ስራ ሲገቡ አርሶ አደሩ ይበልጥ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት የአካባቢው ኅብረተሰብ የገበያ እድል እንዲያገኝም ያደርጋል» በማለት ፓርኩ ለአካባቢው ኅብረተሰብ ተጠቃሚነት ያለውን ፋይዳ ያስረዳሉ፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ከልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ በበኩላቸው፣ በተቀናጁ የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት የተከናወኑ ተግባራት ከአርሶ አደሮች ጋር ያለውን ትስስር በማሻሻል አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ስለማስቻላቸው ያብራራሉ፡፡ እሳቸው እንደሚሉት፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በተገነቡባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ በርካታ አርሶ አደሮች ምርቶቻቸውን በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ገብተው ለሚያለሙ ድርጅቶች በማቅረብ የተሻለ የገበያ ጥቅምና የአቅም ግንባታ ድጋፍ እያገኙ ነው፡፡

ለአብነት ያህል ጅማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከአቮካዶ ዘይት የሚያመርተው «አክሻይ ጄይ» ኩባንያ (Akshay Jay Oil) ከአካባቢው አርሶ አደሮች ጋር ስምምነት ፈፅሞ ምርታቸውን ይቀበላል፡፡ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የቢራ ብቅል የሚያመርተው «ሱፍሌ ማልት ኢትዮጵያ» ፋብሪካ (Soufflet Malt Ethiopia) ከ70ሺ በላይ ከሚሆኑ የአርሲና የባሌ አካባቢ አርሶ አደሮች ጋር ትስስር ፈጥሮ እየሰራ ይገኛል፡፡ ወደ ደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ የገባው «ቡርትማልት» ኩባንያ (BOORTMALT) ደግሞ ከ50ሺ በላይ ከሚሆኑ የአካባቢው አርሶ አደሮች ጋር የገበያ ትስስር ፈጥሯል፡፡

# ጎሜ

# «ኔት ወርክ የለም»?

**አሲሴሮ**

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ወደተለያዩ አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሄደ ሰው በተደጋጋሚ ከሚያደምጣቸው ቃላት መሃል ‹‹ኔት ወርክ የለም ››የሚለውን አባባል የሚስተካከል ያለ አይመስለኝም፡፡ ግብር ለመክፈል ኔት ወርክ የለም፤ የኤሌትሪክ ቢል ለመክፈል ኔት ወርክ ለም፤ የውሃ ቢል ለመክፈል ኔት ወርክ የለም፤ የቤት ኪራይ ለመክፈል ኔት ወርክ የለም፤ ብር ከባንክ ለማውጣትና ለማስገባት ኔት ወርክ የለም ብቻ በአጠቃላይ ኔት ወርክ የለም የሚለው ቃል ሀገሩን አጥለቅልቆታል፡፡

በእርግጥ ይህ ሁሉ ኔት ወርክ የለም የምር ኔት ወርክ ስለሌለ ነው ወይስ ሰነፎችና ሙሰኞች የፈጠሩት ማምለጫ ? የሚለውን መፈተሽ ይገባል። እንደ እኔ ግን አልፎ አልፎ ከሚያጋጥመው የኔት ወርክ መቆራረጥ ውጪ በረባ ባልረባው ኔት ወርክ የለም በሚል ሰበብ አቅመ ደካሞችና አካል ጉዳተኞች ሳይቀሩ ‹‹ነገ ና፤ ከነገ ወዲያ ና›› በሚል ተገልጋይን ከፊት ለማራቅ የሚደረግ ሙከራ የሚበዛ ይመስለኛል፡፡

አብዛኞቹ አገልግሎት ሰጪ ተቋሞቻችን ለደንበኛ አገልግሎት ክብር ስለሌላቸው ተገልጋይን ከፊት ማራቅን እንደ አንድ ስልት ሲጠቀሙበት ማየት የተለመደ ነው፡፡ ለተቸገረ ደንበኛ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ችግሩን ተሸክሞ ከቢሮ ወጥቶ እንዲርቅ የማድረግ ስልትን ይጠቀማሉ፡፡ በአግባቡ ከመነጋገርና ችግርን ከመፍታት ይልቅ ‹‹አይሆንም፤ አይቻልም›› የሚሉ ሃሳችን በመደርደር ደንበኛ መፍትሄ ሳያገኝ እንዲሄድ ማድረግ የተለመደ ነው።

አብዛኞቹ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አርፍዶ በመግባትና ቶሎ በመውጣት፤ ሕዝብን በማጉላላት፤ ምልጃ በመጠየቅ፤ በትውውቅና ዘመድ አዝማድ መስራት፤ በማመናጨቅ ጭምር የተገልጋይን ቆሽት የሚያደብኑ መሆኑን የደረሰበት ያውቀዋል፡፡ ብዙዎችም ‹‹ሰው ጤፉ›› የሚባሉ አይነት ናቸው፡፡

አገልግሎት አሰጣጥ ሳይንስ ነው፤ ጥበብ ነው አልፎ ተርፎም ተሰጥኦንም የሚጠይቅ ሙያ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ቅንነትን ይፈልጋል፡፡ የደከሙ እናቶችን፤ አካል ጉዳተኞችን፤ እርጉዞችን እየተመለከተ ግድ የማይሰጠው ሰራተኛ ወይም ኃላፊ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥበብ ገብቶታል ማለት አይቻለም፡፡ ወይም ደግሞ አገልጋይ ነኝ ብሎ ራሱን መቁጠር አይችልም፡፡

ይህ ሰው ሳይንሳዊ እውቀቱ ቢኖረውም ቅንነት ካልታከለበት በመደበኛ ትምህርት ቤት ገብቶ የቀሰመው ዕውቀት የጋን ውስጥ መብራት ከመሆን አያልፍም፡፡ ከራሱ ተርፎ ለማኅበረሰቡ ጠብ የሚል ነገር የለውም፡፡

በርካታ ተቋማት የስነምግባር መርሆች ብለው መግቢያ በራቸው ላይ ዝርዝር ነጥቦችን በማስታወቂያ መልኩ ይለጥፋሉ፡፡ 12 ስነ ምግባር መርሆች ተብለውም ይታወቃሉ፡፡ ከእነዚህ ስነ ምግባር መርሆች ውስጥ በተራ ቁጥር አንድ የሚቀመጠው ቅንነት ነው፡፡ ቅንነት የሁሉም ነገር መሰረትና መነሻ በመሆኑ ቅድሚያ መሰጠቱ አግባብ ቢሆንም አተገባበሩ እና ክትትሉ ላይ ግን ጥያቄ የሚነሳበት ነው፡፡

ቅንነት ተራ ቁጥር አንድ ሆኖ እንደተቀመጡ የትኛው ሰራተኛ ነው በዚህ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ በቅንነት አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ የሆነው። እንደፋሽን በየቦታው የበዛው ‹‹ኔት ወርክ የለም›› የሚለው ምላሽስ ምን ያህል እውነተኛ ነው፡፡ ወይንስ ተገልጋይን ለማራቅና ለሙስና ለማመቻቸት ከቅንነት ውጪ እየተሰራ ያለ ስራ ነው፡፡

በየቦታው ተዘዋውሮ ለተመለከተው ሕብረተሰቡ ከተማረረባቸው ቃላት ውስጥ ‹‹ኔት ወርክ የለም ›› የሚለው ቀዳሚው ነው፡፡ ‹‹ኔት ወርክ የለም ››የሚለውን ቃል የሚሰማ ተገልጋይ ወሽመጡ ቁርጥ ይላል፡፡ ጉዳዩን ጨርሼ ቶሎ ወደ ስራዬ እመለሳለሁ ብሎ ያሰበ ሁሉ ፊቱ በሀዘን ድባብ ይዋጣል፡፡ ኔት ወርክ እስኪመጣ ድረስም ወዲህ እና ወዲያ እያሉ መጠበቅም ግድ ይሆንበታል፡፡ በአጠቃላይ ኔት ወርክ የለም የሚለው ከንግግሩ ጀምሮ ይዟቸው የሚመጣው መዘዘም ሁሉ አሰልቺዎች ናቸው፡፡

> **ኔት ወርክ መጥፋትን እንደ ሰርግ የሚቆጥሩ ስተቀመጡበት ቦታ የማይመጥኑ ሰነፍ እና ሙሰኛ ሰራተኞችና አመራሮችም አሉ**

ከሁሉ የከፋው ደግሞ ጠፋ የተባለው ኔት ወርክ የሚመጣበት ጊዜ አለመታወቁ ነው፡፡ ደቂቃዎችን ይቆይ ሰዓታትን አለፍ ሲልም ቀናትን ሊቆይ ይችላል፡፡ ይህንን የሚያውቀው አንዳንድ ጊዜ ቴሌ ብዙ ጊዜ ግን አገልግሎቱን የሚሰጡት ሰራተኞች ናቸው፡፡ የአገልጋይነት መንፈሱ ያላቸውና ቅን የሆኑ አገልጋዮች ኔት ወርክ ጠፋ ሲባል እነሱም ይጨነቃሉ፤ የተገልጋዩ እንግልት ይሰማቸዋል፡፡

የኔት ወርክ መጥፋትን እንደ ሰርግ የሚቆጥሩ ለተቀመጡበት ቦታ የማይመጥኑ ሰነፍ እና ሙሰኛ ሰራተኞችና አመራሮችም አሉ፡፡ አጋጣሚውን በመጠቀም ከቢሮ ሾልኮ ለመውጣትና የራሳቸውን ጉዳይ ለማከናወን ሲጠቀሙበት ይታያል። አንዳንዶቹም በተሽከርካሪ ወንበራቸው ላይ ተቀምጠው ስልካቸውን መነካካት ደስታ ይሰጣቸዋል፡፡

ብዙዎች እንደሚናገሩት ግን ሲስተሙን በመነካካት ኔት ወርክ እንዲጠፋና ሕብረተሰቡ እንዲጉላላ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ተገልጋዩ ሲጨንቀው በሙስና ጉዳዩን ለማስጨረስ ይገደዳል፡፡ ሙሰኞችም ስራቸውን ያጧጡፋሉ፤ ኪሳቸውን ያደልባሉ፡፡ ስለዚህም ኔትወርክ የለም የሚለው አባባል ለሙሰኞች የማይደርቅ የገቢ ምንጭ ሆኗል ማለት ነው፡፡

አንድ ጓደኛዬ የገጠመውን እዚህ ጋር ባነሳ ለዚሁ አባባሌ ማሳያ ይሆንልኛል፡፡ ጓደኛዬ ነጋዴ ነው፡፡ እንደልማድ ሆኖበት ግብር የሚከፍለው በመጨረሻዎቹ ቀናት ነው፡፡ ይህንን የሚያውቁ የገቢ መስሪያ ቤቱ ሰራተኞች በመጨረሻዎቹ ቀናት ኔት ወርክ የለም በሚል ስራ ያቆማሉ፡፡ ጓደኛዬም የሚመጣበትን ቅጣት እያሰበ ይጨነቃል፡፡ ቅጣቱ ደግሞ ከፍተኛ ከመሆኑም ባሻገር ብዙ መጉላላትን የሚያስከትል ነው፡፡ የጨነቀው እርጉዝ ያገባል እንደሚባለው እሱም ሆነ ሌሎች ነጋዴዎቹ ጉዳያቸውን በምልጃ ለማስፈጸም ይገደዳሉ፡፡

ይኸው የእኔ ጓደኛም በተደጋጋሚ በዚህ መልኩ ጉዳዩን እያስፈጸመ ይገኛል፡፡ ኔት ወርክ የለም የሚለው አባባልም ተገልጋይን አጣብቂኝ ውስጥ ለመክተት የተዘረጋ ስልት ነው ይላል፤ በተደጋጋሚ ከደረሰበት ችግር በመነሳት፡፡ ስለዚህም ‹‹ኔት ወርክ የለም›› ሲባል እውነት ነው ወይ ? የሚለውን መፈተሹ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ካልሆነም ተገልጋዩ ኔት ወርክ መሄዱን የሚያረጋግጥበት መንገድ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን አሁንም በኔት ወርክ የለም ሰበብ ብዙዎች ለሙስና መጋለጣቸው አይቀሬ ነው፡፡

ውጤቱን በጉጉት እና በተስፋ ለሚጠብቅ ተስፈኛ ሕዝብን ኔት ወርክ የለም በሚል ተስፋ እንዲቆርጥ ማድረግ ምን ያህል ኢሞራላዊ ድርጊት እንደሆነ የደረሰበት ሁሉ ያውቀዋል፡፡

ግልጽ የሆነ አገልግሎት ለአገልግሎት ፈላጊው ሕዝብ ማቅረብ ግዴታ ሲሆን ለተገልጋዩም መብት ነው፡፡ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 12 እንደተደነገገው የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 12/2/ "ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል" በማለት ደንግጓል፡፡

ከዚህ ሕገመንግስታዊ አንቀጽ የምንማረው አገልጋዩ ለተገልጋዩ መስጠት የሚገባውን አገልግሎት የሚሰጥበትን አሠራር ካልዘረጋ፣ በዘረጋው አሠራር መሠረት አገልግሎት ለመስጠት የገባውን ቃል ግልጽነትና ጥራት ባለው መንገድ ካልሠጠ እና የመንግሥት ሕጎችን፣ ደንቦችን መመሪያዎችንና አሠራሮችን ካልፈፀመ ወይም ካላስፈፀመ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

በዚህ መሠረት ሊሠጥ የሚገባው አገልግሎት ቃል ለተገባለት ሕዝብ/ዜጋ መድረስ አለመድረሱ ሲጋለጥ ቃሉን የጠበቀና ያሳካ የሚመሰገንበት፣ የሚበረታታበትና የሚሸለምበት አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡ በአንጻሩ በገባው ቃል መሠረት ያልፈፀመ የሚመከርበትና የሚወቀስበት እንዲሁም ሆን ብሎ ያጠፋ ከሆነ ሕጋዊ ሥርዓቱን ተከትሎ የሚጠየቅበትና የሚቀጣበት ሥርዓት በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

የዚህ መርህ መሠረታዊ ቁምነገር ዜጎች በቂ መረጃ ያላቸው ሆነው ተገቢውን አቋም መያዝ የሚያስችላቸው መሆኑ ዋንኛው ጉዳይ ሆኖ መረጃ በማጣት ምክንያት ያለአግባብ የሚፈጠር አለመግባባት፣ አለመተማመንና ጥርጣሬን ከማስወገዱም በላይ ስህተትን በቀላሉ ለማወቅና ለመፍታት የሚችልበት ሁኔታን መፍጠሩ ነው። አገልግሎትን ለተገልጋዩ ግልጽ ማድረጉ ኔት ወርክ የለም እያሉ ለሚያጭበረብሩትም መፍትሄ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ግልጽነትን ከማስፈን ባሻገር ቢያንስ የእያንዳንዱን ተቋም አሰራር መፈተሽ፤ መከታተልና መደገፍ የመንግስት አንዱ የትኩረት አቅጣጫ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንጻር ሰሞኑን የመንግስት ከፍተኛ ስራ ኃላፊዎች እያደረጉት ያለው የክትትልና ድጋፍ አካሄድ የሚበረታታ ነው፡፡

የመንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ከከተማ እስከ ገጠር በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በሚባል መልኩ አርሶ አደሩ ድረስ በመውረድ ምልከታ እያደረጉ ነው፡፡ የመንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች እያደረጉት ያለው ምልከታ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎች ያሉ ሐብቶችና ጸጋዎችን በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል እና የሚነሱ ቅሬታዎችንም ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀራርቦ ለመፍታትም በር የሚከፍት ነው፡፡

በማንኛውም መንገድ ሕህዝብ መደመጥን ይፈልጋል፡፡ ለጥያቄዎቹ ተግባራዊ ምላሽ ይሻል፤ ካልሆነም ጥያቄዎቹ ምላሽ ያላገኙበትን ተጨባጭ ምክንቶች ማዳመጥን ይፈልጋል፡፡ ይህ ካልሆነ ሰሚ እንዳጣ፤ ተገቢው ክብር እንዳልተሰጠውና እንደተናቀ ሊቆጥር ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ የመጨረሻ ውጤቱ በመንግስትና በሕዝብ መካከል መራረቅን ይፈጥራል፡፡ አሁን አሁን በኔት ወርክ ሰበብ እየተራራቀ ያለውን የአገልጋይና ተገልጋይ ግንኙነት ለመፈተሽም እድል ይሰጣል፡፡

በተለይም በዚህ የቴክኖሎጂና የግሎባላይዜሽን ዘመን ከሕዝብ እርቆ ሀገርን መምራት ከማይቻል ሁኔታ ላይ ደርሰናል፡፡ የእያንዳንዱ ዜጋ ድምፅ ዋጋ እንዳለው ሁሉ፣ የእያንዳንዱ ዜጋም ጥያቄ ዕውቅና መስጠት ሊታለፍ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ ከሕዝብ ፈቃድና ፍላጎት ውጪ የሆኑ ድርጊቶች ተቀባይነት እያጡ፣ በሕዝብ ይሁንታ ላይ የተመሠረቱ ውሳኔዎች ተቀባይነት እያገኙ መሄድ ጀምረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ መለመድ ካለባቸው መልካም ተግባራት ውስጥ የሕዝብ ፈቃድና ፍላጎት ማክበር አንዱ ነው፡፡ አገር በመምራት ላይ ያለው ገዥ ፓርቲም ሆነ ሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ መስጠት ያለባቸው የሥልጣን ሉዓላዊ ባለቤት የሆነውን ሕዝብ ማክበር ነው፡፡

ከሰሞኑ በመንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች አርሶ አደሩ ድረስ በመውረድ እየተደረጉ ያሉ ክትትሎች አንዱ የሕዝብ እውነተኛ ስሜት ማግኛ መንገድ ስለሆነ ተጠናክሮ መቀጠል የሚገባው ነው፡፡

በእርግጥ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት የመሰረተ ልማት እጥረት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ከአቅም ውስንነት አንጻር በየተቋማቱ በቂ ኔት ወርክ ዘርግቶ ተገልጋይን ማርካት ላይቻል ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ ሽፋን ግን ሕዝብን ማጉላላትና አልፎ ተርፎም ለምልጃ ማዘጋጀት ግን ይቅር የማይባል ኃጢያት መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡

የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ተዘዋውሮ መመልከት የቻለ ሰው ኔት ወርክ የለም የሚለው አባባል ብዙዎችን የሚያስበረግግና ተስፋ የሚያስቆርጥ መሆኑን ለመረዳት አያዳግተውም። በኔት ወርክ የለም ሽፋን በርካታ ተገልጋዮች ለእንግልትና አለፍ ሲልም ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋልጠዋልና ሳይቃጠል በቅጠል እንደሚባለው ከወዲሁ የግልጽነት አሰራርን ማስፈን ለነገ የማይባል መፍትሄ ነው፡፡

# የዘመን ጥበብ

## ሙሾ እናውርድ!

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ሙሾ ጥበብ ሙሾ እንጉርጉሮ፤ ለኛ ሲያንጎራጉርና ለውስጣዊ ስሜታችን እላይ ታች ሲል እንዳልከረመ ሁሉ አሁን ለእርሱም በትዝታ የሚያንጎራጉርለትን ሳይፈልግ አልቀረም። ምክንያቱም ከነበረበት የጥበብ ከፍታ፤ ከተሰቀለበት የማህበረሰቡ ልብ ውስጥ ወጥቶ ባይተዋርነት ከተሰማው ዋል አደር ብሏል፡፡ አሁን መሪር እንባዋን የምታፈስለት ጥበብ ናት፡፡ ሀዘኗ ተገልጦ ለአይን የሚታይ ቢሆን ምናልባትም እንባዋን ልክ እንደዚህች ብላቴና እያዘራችው ይሆናል፡፡ ድሮ ድሮማ የማህበረሰቡ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ሁሉ በሙሾ የተዋዛ፤ የት አለ ሙሾ የሚያስብል ነበር፡፡

እቤት ውስጥ አባት ከልጁ፤ ሚስት ከባሏ፤ ጎረቤት ከጎረቤቱ፤ አዙሮ ለመናገር የፈለገውን ነገር ሁሉ በቅኔ እያሾረ የሚገልጸው በሙሾ ነበር፡፡ በየስብሰባና እድሩ ሙሾ ያለምንም አጀንዳ ሁሌም ድባቡን ይዘውራል። በየሥርግና ማህበሩ ሁሉ ከጠላና ጠጁ ቀጥሎ የሚቀዳው ሙሾው ነው፡፡ በባህሪው፤ የሀዘንና የመሪሪ እንባ አቁማዳ ብቻ አይደለም፡፡ አንዳንድ ጊዜም አፈንጋጭነቱ የተለየ ነው፡፡ የማይገባበትና እየያዘ የማይጥለው ጥበባዊ የስሜት አንጓ የለም፡፡ በሙሾ ውስጥ የሞተ ሰው ብቻ ሳይሆን ከሰማይ እስከ ምድር፤ ከሰው ልጆች እስከ ፈጣሪ፤ ከነፍሳት እስከ ግኡዝ አካላት፤ ከክዋክብት እስከ ዘመንና የጊዜ መዘውሮች፤ ለሁሉም ሙሾ ይወረድላቸዋል፡፡

ሀዘን፣ ቅሬታ፣ ንዴት፣ ስላቅ፣ አሽሙር፣ ምስጋና፣ ደስታ፣ ፍትህ፤ እውነት...ሁሉም ማህበራዊ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ይንጸባረቁበታል፡፡ አንዳንዴ፤ ሙሾ ምን መልክ አለው? ብሎ ከመጠየቁ የሌለውን መጠየቁ የሚቀል ነው፡፡ አንዱ ሙሾ የተሠራው፤ ከሦስት የጥበብ ልጆች ዘረመል ነው፡፡ የመጀመሪያው ግጥም ነው፡፡ ሙሾ ያለግጥም አይወርድም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የዜማን ዘረመል እናገኛለን፡፡ ግጥሙ እንዳለ፤ ዜማው ከሙዚቃ ጋር የሚያመሳስለውን ነገር ይፈጥራል፡፡ ጥበባዊ ይዘቱ ጎልቶ እንዲታይ የሚያደርገው ሦስተኛው ነገር ቅኔው ነው፡፡ በቅኔ የተለወሰ ሙሾ ማለት በቅቤ እንደተለወሰ ‘ጭኮ‘ ማለት ነው፡፡ ከመጣፈጡም ዘመን ተሻጋሪነቱ ከፍ ያለ ነው፡፡

በአጠቃላይ ማንነቱ ከብዙ የጥበብ ትውፊቶች ለየት የሚያደርገው ነገር፤ እያንዳንዱ የሙሾ ግጥም፤ ዜማና ቅኔዎች በምክንያትና ከእውነት ወንዝ ላይ የሚቀዱ መሆናቸው ነው፡፡ ማህበረሰቡ ሙሾ በሚያወርድበት አጋጣሚ ሁሉ የተፈጠረ ክስተት ከበስተጀርባው ይኖራል፡፡ በሙሾ ቤት ውስጥ ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛው ነገር፤ ሙሾ አውራጁ ከማውረዱ በፊት ስለሚለው ጉዳይ ብዙ አውጥቶና አውርዶ እውነታውን አጢኖ የሚፈጥረው ነው። ለምሳሌ፤ በለቅሶ ቤት እየተከፈላቸው በሚሠሩ አስለቃሾች ዘንድ የሚታይ ነው፡፡ ግጥሞቹ የሟችን እውነተኛ ማንነት፤ ዕድሜ፤ ጾታ፤ መልክ ባህሪ፤ የኑሮ ደረጃና መሰል ጉዳዮችን ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅበታል። ሁለተኛው ደግሞ፤ ስለምንና እንዴት ብዬ...በማለት ተጨንቆና ተጠቦ የሚፈጠር ሳይሆን ለአንድ ለተፈጠረ ነገር ውስጣዊ ስሜትን በውጫዊ ቃላት ለማንጸባረቅ በድንገት ጣል የሚደረግ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ሙሾ የሚወርደው በቅኔ ዘረፋ ነው፡፡ ለማለት የፈለጉትን የሚያመለክቱት በውስጠ ወይራ ዘንግ ነው፡፡ ከስሜት የመነጨ እንደመሆኑ መልእክቱም ጠጣርና ከበድ ያለ ነው፡፡

ሙሾ ያለምክንያት አይወርድም፤ ቅኔውም ያለ ቦታው አይፈስም ብለናል፡፡ በሀገራችን ታሪክ ውስጥ ሆኑ ተከሰቱ ከተባሉት ከእያንዳንዱ ክስተቶች በስተጀርባ ሙሾ አለ፡፡ ጥቂቶቹንም እንደማሳያ እንመልከታቸው፡፡ ደርግ የንጉሡን ዘውድ ገርስሶ በመጣበት ወቅት በጎንደር አካባቢ ይኖር የነበረው መላኩ ተፈራ የተባለው ሰው ግን አብዮቱን አልታዘዝም በማለት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶችን ረሽኖ በማስረሸን ጭካኔው የታወቀ ነበር፡፡ የጎንደር እናቶችም እንዲህ ሲሉ የዜማ ሙሾ አወረዱለት፤



**«መላኩ ተፈራ የእግዜር ታናሽ ወንድም**
**የዛሬን ማርልኝ የነገን አልወልድም»**

የሙሾ ጥበብ የማይረሳውን መልኩን ያኖረበት ክስተት የአጼ ምኒልክ ሞት ነው፡፡ በጊዜው ንጉሡ የሞቱ ቢሆንም የቤተ መንግሥቱ ሰዎች ግን ነገሮች ፈር እስኪይዙ ድረስ በማለት ሀዘኑንም መርዶውንም አምቀውት ለመቆየት ሞከሩ፡፡ ጭምጭምታው ግን ከውጭ ወጥቶ ስር ስሩን ይሄድ ነበርና “እምዬ..ጌትዬ... አባቴ...” እያለ ከየቤቱ ሆኖ የሚያለቅሰውም ብዙ ነበር። ከእዚህ መሃከልም ቤተ መንግሥቱ ድረስ የዘለቀ አንድ አልቃሽ እንዲህ ሲል ሙሾውን አወረደው፤

**«ፈረስ በቅሎ ስጠኝ ብዬ አለምንህም**
**አምና ነበር እንጂ ዘንድሮ የለህም»**

በማለት ሕዝቡ ስለ ንጉሡ ሞት ማወቃቸውን አፍረጠረጠው፡፡ በዚሁ ለቅሶ ወቅትም እቴጌ ጣይቱ ሌላ ታሪካዊ ሙሾ አወረዱ፡፡

**«ነጋሪት ማስመታት፤ እምቢልታ ማስነፋት ነበረ ሥራችን**
**ሰው መሆን አይቀርም ደረሰ ተራችን»** ሲሉ ሀዘናቸውን ገለጹ፡፡

በአጼ ምኒልክ ሞት ምክንያት ይዘንቡና ይጎርፉ የነበሩት የሙሾ ግጥምና ዜማዎች በገፍ ቢሆኑም፤ ከዚህች ግጥም ግን ጥቂት ስንኞችን ቆንጥረን እንመልከተው፡፡ የሙሾው ግጥም ተጽፎ የሚገኘው “ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት” ከሚለው መጽሐፍ ላይ ሲሆን ባለቤትነቱ ደግሞ ቀጣዩን የንግሥና ዘውድ የጫኑት፤ የንግሥት ዘውዲቱ ነው፡፡

**«እልፍ ነፍጥ በኋለው፤ እልፍ ነፍጥ በፊት፣**
**ባለወርቅ መጣብር አያሌው ፈረስ፣**
**ይመስለኝ ነበር ይኼ የማይፈርስ፡፡**
**ብትታመም ልጅህ እጅግ ጨነቀኝ፣**
**ብትሞትስ አልሞትም እኔ ብልጥ ነኝ፡፡**
**ቀድሞ የምናየው የለመድነው ቀርቶ፣**
**እንግዳ ሞት አየሁ ካባቴ ቤት ገብቶ፡፡**
**አሻግሬ ሳየው እንዲያ በሰው ላይ**
**መከራም እንደሰው ይለመዳል ወይ፡፡»**

እንግዲህ እኚህና እኚህን መሰል በዘመን ርቀት ያልተገቱ የሙሾ ጥበቦች፤ በአንድ ወቅት የነበረን ታሪክ ቁልጭ አድርገው የሚናገሩና ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ በመሆናቸው ታሪክ ነጋሪነታቸው ላቅ ያለ ነው፡፡ በጥቂት ቃላት፤ በጥቂት ስንኞች ግዙፉን ታሪክ ከነ ነብሱ ያኖሩታል፡፡ አሁን ሙሾ የሚያስወርድ ሕይወት ጠፍቶ ሳይሆን የጠፋው ሙሾ አውራጁ ነው፡፡ በአብዛኛው ሰው አረዳድም፤ ሙሾ ለሙታንና በሙታን መንደር ብቻ የሚቀርብ የሀዘን ንፍሮ መስሎ ይታያል፡፡ ዳሩ ግን ይህ አንዱ እንጂ ብቸኛው አይደለም፡፡ ከዚህ የላቀ አንደምታ አለው፡፡ በእርግጥ በአንደኛው ዘመን፤ ከማህበረሰቡ ጋር ያለው ቁርኝት እየቀነሰ ሲመጣ ግብሩ ለለቅሶና ለእንባ እየዬነት ብቻ ነበር፡፡ እንደዛሬው ከሁሉም ሳይጣላ በፊት፡፡ በጥንቱ ዘመን፤ በተለይ በ1880ዎቹ በኢትዮጵያ፤ ከሰሜን ሸዋ አካባቢ በዛወርቅና ፍትግ የተባሉ ሁለት የሙሾ ጠቢባን ስለመኖራቸው ይነገራል፡፡

ከ1880-84 በነበረው ከባድ ድርቅ፤ ሰውና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ከብቶችም ያለቁበት ነበርና በየገበያው ሁሉ እየዞሩ ይሄን ሙሾ ያወርዱት ነበር። በቅርብ ርቀት ካሉት፤ የሙሾ ግጥምን በመጠቀም ደረጃ ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህንን የሚስተካከል የለም። ቢገባን ሙሾ የኋላ ቀርነት መገለጫ ተድርጎ የሚጣል አልነበረም፡፡ ከኋላ ሆነን የፊቱን ለማየት የተሳነንስ እኛው ነን፡፡ ድሮም ሆነ ዘንድሮ ኋላ ቀርነት ነው ብለው የሚሟገቱ ሰዎች የሚያነሱት ነጥብ ቢኖር “ሀዘንን እያባባሰ፤ ለጉዳት ይዳርጋል” የሚል ነው፡፡ ምርትና ግርዱን ካለየን ስንዴም ቢሆን ለመብላት የሚሆን አይደለም፡፡ የመጀመሪያው ስህተት ሙሾ ለሀዘን ብቻ የምንጠቀመው የሀዘን መወጣጫ አድርጎ ማሰቡ ነው። ሁለተኛው ስህተት ደግሞ፤ በትልቁ ነጭ ወረቀት ላይ ያለውን ትንሽ ጥቁር ነጠብ ተመልክቶ፤ ትንሹን ስህተት ከማረም ይልቅ፤ ትልቁን የጥበብ ብራና መቅደዱ ነው፡፡

ኪነ ጥበባዊ ፋይዳውን ትተን በሀዘን ቤት ስላለው ጠቀሜታ ብንመለከት እንኳን፤ ከጉዳቱ ጥቅሙ የሚያመዝንባቸው ሁኔታዎችም አሉ፡፡ በሞት ዳፋ ወደ መሪር ሀዘን ገብቶ በእንባ ማልቀሱ ይህ የማይሻር የሰው ልጆች ባህሪ ነው፡፡ በእንደነዚህ አይነት ከባድ ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖ በአግባቡ ማልቀሱን፤ ተፈጥሮም ሆነ ሳይንሱ የሚመክሩት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም እንባ የታመቀውን ውስጣዊ የሀዘን ክምችት የመበተንና ቀለል እንዲለን የማድረግ ኃይል ስላለው ነው፡፡ “አልቅስና ይውጣልህ” የምንለውም ለዚሁ ነው፡፡

መሆን የሌለባቸው፤ ደረት መደለቁና ከመሬት ላይ መፍረጡ እንዳሉ ሆነው፤ የሙሾ ግጥምና ዜማዎች ልብን የሚነኩ እንደሞሆናቸው፤ ለዘለዓለሙ ባይሆንም የሀዘንተኛውን የልብ ሸክም በእንባ ታጥቦ እንዲወጣ ያደርጋሉ፡፡ የውዳሴና የምስጋና እንዲሁም ሟችን ህያው የሚያደርጉ ልዩ ልዩ ስንኞችም ይኖሩታልና። በተቃራኒው ደግሞ የመጽናናትን ኃይልና ብርታት ይሰጣሉ፡፡ ሙሾን የኋላ ቀርነት መገለጫ ካደረግነው፤ ይሄ ሁላችንንም የሚያስማማ ሳይሆን የሚያጋጭ ነው። በእርግጥ ሁላችንንም ሊያስማማን የሚችል አንድ ነገር ቢኖር፤ በሙሾ አካል ላይ ተለጣፊ ሆነው የገቡት ባዕዳን ግብሮች ናቸው፡፡

የሙሾ ጥበብ ውበትና ጥፍጥናው የሚገኘው ከውስጣዊ የስሜት ቋታችን ነው፡፡ የግጥምና ዜማ ቅኔው ሁሉ የሚሠራው ከስጋችን ጠለቅ ባለው የነብሳችን አድባር ላይ ነው፡፡ እኒህ ባዕዳን ያልናቸው እንደ ደረት መደለቅ፣ ጸጉር መቧጠጥ፣ ሰውነትን መቦጫጨር፣ ከመሬት እየተነሱ መፍረጥ...ስንመለከታቸው አካልን ከመጉዳትን ሌላ የህመም ስሜት ከመጨመር ውጭ ይሄ ነው የሚባል በማስረጃ ሊደገፍ የሚችል እውነታ የላቸውም፡፡ ልንስማማ የምንችለውም በእነዚህ ባዕዳን ግብሮች መቅረት ላይ ነው፡፡

ሙሾ ጥበብ በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች እንደ ባህልና ወጉ በተለየ መንገድ የሚከወን ቢሆንም በተለየ መንገድ የሚነሱ ደግሞ አሉ፡፡ ለአብነትም እንቅስቃሴያዊ የሙሾ ስልትን ድራማዊ በሆነ መንገድ የሚጠቀሙ ሁለት አካባቢዎች የነበሩ መሆናቸው ነው፡፡ የመጀመሪያው ደቡብ ጎንደር አካባቢ ነው። ሟች ወንድ በሚሆንበት ጊዜ መጠኑ ከፍ ያለ ይሁን እንጂ በሴቶቹም አለ፡፡ ፉከራው፤ ሽለላው፤ የግጥምና ዜማው እንጉርጉሮ፤ በአጠቃላይ በአንድ መራሄ ተውኔት ተዘጋጅቶ የቀረበ እንጂ ባላገሩ እዚያው በዚያው ባህላዊውን ግብሩን እየከወነ ያለ አይመስልም። ሌላኛውና ሁለተኛው የሙሾ ድራማዊ ስልት ወደ ጉራጌ ዞን የሶዶ ክስታኔ ማህበረሰብ ይወስደናል፡፡ በማህበረሰቡ ለረዥም ዘመናት ጠንከር ያለ የባህል ልማዶች ከሚከወንባቸው ስፍራዎች አንደኛው የለቅሶ ሥርዓት ነው፡፡

እንቅስቃሴያዊውን የሀዘን መግለጫ ሥርዓታ ቸውን ስንመለከት ድራማዊ የኬሮግራፊ እንቅስቃሴን እናስተውልበታለን፡፡ የሟች ዘመድ አዝማድ በተለይም ሴቶቹ በአንድ ቦታ ላይ ሰብሰብ ብለው ይቆማሉ። በመሀላቸው ከበሮ ይዛ የምትቆመዋ ሴት ከበሮውን እየደለቀች፤ ግጥሙን እያወጣች፤ በሀዘን ቅላጼ ሙሾውን ታወርደዋለች፡፡ በዚህ ጊዜም ወንዶቹ፤ ከሴቶቹ በሌላ አቅጣጫ ወይንም በስተኋላ፤ በሦስት አሊያም በሁለት እረድፍ ተሰልፈው በመቆም በእኩል እንቅስቃሴ ወደፊትና ወደኋላ እያሉ ሀዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡ እንደነዚህ አይነቶቹ የሙሾ ሥርዓቶች፤ በሀዘን የሚገነፍለውን ውስጣዊውን ስሜታችንን ሰከን የሚያደርጉ በመሆናቸው፤ በኃይል እራስን የመጉዳት አደጋዎችን ይቀንሳሉ፡፡ እንግዲህ በዋናነት የሚታወቁበት አካባቢዎች እንዳሉ ሆነው፤ በየትኛውም የሀገራችን ክፍል ጥበብን ያላዘለ የሙሾ ሥርዓት ነበር ለማለት ያዳግታል፡፡ ሁሉም ግን አሁን ከመኖር ወደ አለመኖር ተሸጋግረዋል፡፡ እንዴት ያለውን ጥበብ ይዘው፤ እንዴት እንደጣሉት እነርሱም ሳይገባቸው ሹልክ ብሎ ወጥቷል፡፡

ከሁሉ አስቀድሞ በመጀመሪያ፤ ይህ ታላቅ ጥበብ በቀደመው ዘመን በሁሉም እጅ የነበረ እንቁ ነበር፡፡ ማኅበረሰቡም አዘውትሮ በየዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው ሁሉ ይጠቀመው ነበር፡፡ ከኛ ቀደም ብለው በነበሩት ትውልዶች እየተቀዛቀዘ ሄደ፡፡ የቀድሞ ወጉን እያጣ መጣ፡፡ በኛ ትውልድ መጀመሪያና በእነርሱ መጨረሻ ደግሞ የሁሉም መሆኑ ቀርቶ ለጥቂቶች የተሰጠ ተሰጥኦ ተደርጎ ተቆጠረ፡፡ በእጃቸው የቀረው እነዚህ ጥቂት ባለተሰጥኦዎች ወደ ሙያነት ቀየሩት፡፡ ሙሾ አውራጅ፤ አስለቃሽ እየተባሉ በዚሁ የታወቁና ተፈላጊ የነበሩ ምርጥ አስለቃሾችም ታይተውበታል። ሙያና ሥራዬ ብለው በዚህ ብቻ ቤተሰቦቻቸውን ሲያስተዳድሩ የነበሩ ብዙ ናቸው፡፡ በሠርጉ ጊዜ አቧራ የሚያስጨሱ፤ አሉ የተባሉ አጫፋሪዎች እንደሚፈለጉ ሁሉ፤ በሀዘኑም ወቅት አስለቃሽ ሙሾ አውራጆችን መፈለጉ ተለመደ፡፡ በተለይ ደግሞ ታላላቆቹ ሲሞቱ። ሳር ቅጠሉንም እየያዘ፤ እንደምንም ሲፍገመገም ከዚህኛው ጊዜና ትውልድ ላይ ሲደርስ ግን፤ ‘አንተ ኋላ ቀር‘ በሚል ዱላ ቋንጃውን ተመቶ በአፍጢሙ ወደቀ። የተመታው እንዳይድን እንዳይሽር ተደርጎ ቢሆንም ስለመሞቱ ግን...

ሙሾ ትልቅ ጥበብ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ሙሾ ግን ዛሬም በሕይወት አለ ወይ? የሚለው ጥያቄ ከማከራከሩም ለፍርድም የማያመች ነገር ነው፡፡ የለም እንዳንል መልኩን እየቀያየር በሌሎች የጥበብ ሥራዎች ውስጥ እንደማጣፈጫ ሆኖ ሲገባ እናየዋለን፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከደራሲያኑ፤ ከሙዚቀኞቹ፤ ከፊልምና ቲያትረኞቹ ቤት አልፎ አልፎም ቢሆን ጎራ ሲል ይስተዋላል፡፡ እንደ ጥለት ማሳመሪያ የሚገቡት እነዚህ ቅንጭብጭብ የሙሾ ክሮች መደወራቸው መልካም ሆኖ ሳለ፤ እራሱን ችሎ እንዲታይ አለመደረጉ ግን በደል ነው፡፡ ደግሞ እግር ጥሎን ድንገት፤ ከአንድ አካባቢ በአንድ አጋጣሚ እንመለከተዋለን። በእንጉርጉሮ የዜማ ስልቶች ውስጥም ብቅ ጥልቅ ሲል ማየቱ የተለመደ ነው፡፡ ለዛሬው መኖሩ ዋስትና ባይሆኑም፤ በድሮው ጊዜ የነበሩና አሁንም ድረስ ተጽፈው የሚገኙ እጅግ በርካታ የሙሾ ጥበቦችም አሉ፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር ስለመኖሩ የሚታወቀው ስለነበረ ሳይሆን ዛሬም በአደባባይ ሲከወንና ሲተገበር ስናይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ዛሬ ላይ የለም፡፡ የእውነትም ሞቶ ከሆነ ግን ጥበብ ስለመሆኑ አምነን ተቀብለን የሚገባውንም ጥበባዊ እውቅና ሳንሰጠው በመሆኑ ሀዘኑ በእንባም የሚወጣ አይደለም፡፡ የጥበብ የልብ ስብራትም የሚጠገን አይሆንም፡፡

ለስንቱ ስታለቅስ እንዳልኖርክ አሁን ላንተ የሚያለቅስ ጠፋ? ከዚህ ሁሉ ሰው እንዴት ላንተ የሚሆን፤ ለሙሾ ሙሾ እናውርድ የሚል ሙሾ አውራጅ...ግጥሙን ከዜማው አድርጎ የሚያንጎራጉርልህንስ አጣህ? ቅኔውን እየዘረፈ የሚያበላህስ? ኸረ እንዲያው ሌላውን ሁሉ ተወውና፤ የሚያስታውስህስ ይኖር ይሆን? አይ ሙሾ ምስኪኑ!...ብኩን ጥበቡ፡፡

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ይቻላልን በተግባር

**እየሩስ ተስፋዬ**

ዓይነ ሥውራንን ጨምሮ ሌሎች አካል ጉዳተኞች በትምህርት፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ፣ በሥራ እና በሌሎች የአካታችነት እጦት ችግር ሳቢያ ተሳትፏቸው አናሳ እንደሆነ በተደጋጋሚ ይገለፃል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በመሠረተ ልማት፣ በአካታች ትምህርት፣ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ልዩ ችሎታቸውን በመጠቀም፣ የሥራ ዕድሎችን መፍጠር እና መደገፍ እንደሚገባ በመፍትሔነት ከሚጠቀሱት ሃሳቦች መካከል ይጠቀሳሉ። ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም እንዲያገኙና ተሳታፊነታቸውን ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶ መሥራት እንዳለበትም ይነገራል።

እንዲያም ሆኖ አንዳንድ አካል ጉዳተኞች ችግሮች ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ መፍትሔ ላይ ይበረታሉ። የሚያጋጥማቸውን ችግር ወደ ጎን በመተው በጽናት ጉዟቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ደግሞ የተፈጠረላቸውን አጋጣሚም ይሁን ያገኙትን ዕድል በሚገባ በመጠቀም ለብዙዎቻችን አርዓያ መሆን ችለዋል፡፡ የመጡበትን አድካሚ መንገድ ከማሰብ ይልቅ ያለፉበትን ጽናት ለሌሎች ጉልበት ይሆን ዘንድ ያጋሯቸዋል፡፡

ውልደታቸው ጎንደር ልዩ ቦታው ጎርጎራ ይባላል። የወታደር ልጅ ናቸው፡፡ በአምስት ዓመታቸው በኩፍኝ በሽታ ዓይነ ሥውር ሆኑ፡፡ እኚህ ሴት ወይዘሮ ዘነበች በላቸው ይባላሉ፡፡ አባታቸው ዓይናቸው ወደ ቀድሞ ዕይታው እንዲመለስ ብዙ ጥረት አድርገዋል፡፡ በኋላ ላይ ግን አባት ልጃቸውን ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ አመጡ፡፡ አዲስ አበባ በተለምዶ ቀጨኔ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በቀድሞ ስያሜው ‹‹ቀጨኔ የሕጻናት ማሳደጊያ››ን ተቀላቀሉ፡፡ ልጅነታቸውን ያሳለፉት በማሳደጊያው ሲሆን እስከ ሰባተኛ ክፍል የተማሩትም እዛው ነው፡፡ የስምንተኛ ክፍል ትምህርታቸውን በቀድሞ ስያሜው ‹‹እቴጌ መነን



ወይዘሮ ዘነበች በላቸው፣

ትምህርት ቤት›› በአሁኑ ‹‹የካቲት 12 ትምህርት ቤት›› ተከታትለዋል፡፡

እርሳቸው በተማሩበት ወቅት ትምህርት ቤቱ ሴቶች ብቻ ይማሩበት እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ለመምህርነት በቀጥታ ወደ ወላይታ በማቅናት የዓይነ ሥውራን ትምህርት ቤት ማስተማር ጀመሩ። ብዙም ሳይቆይ ትምህርት ቤቱ ተዘጋ፡፡ የተዘጋበት ምክንያት እና የነበረውን አቤቱታ አቅርበው በመንግሥት ቀጣሪነት የመምህርትነታቸውን ሙያ ቀጠሉ፡፡ በዛም ዓይነ ሥውራንን ለአስር ዓመታት ያህል አስተምረዋል፡፡

ከወላይታ ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላም የሥነ ዜጋ መምህርት በመሆን በፀሐይ ጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተምረዋል፡፡ ወይዘሮ ዘነበች በአጠቃላይ ለ35 ዓመታት ያህል በመምህርትነት ማገልገል የቻሉ ሲሆኑ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮም ‹‹ብራይት ወርልድ ፎር ብላይንድ ዉሜን አሶሴሽን›› በተሰኘ የበጎ አድራጎት ድርጅትን በሥራ አስኪያጅነት እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

ወላጆች የልጆቻቸው የወደፊት ሕይወት ያማረ እና የሠመረ እንዲሆን እገዛቸው ባይለይ መልካም እንደሆነ ይታመናል፡፡ የወይዘሮ ዘነበች ወላጆችም በዚህ ረገድ ጥሩ የሚባሉ ነበሩ፡፡ ልጃቸውን በሚገባ ስላሳደጓቸው በልጅነታቸው ይህ ነው የሚባል ነገር አልጎደለባቸውም፡፡ የከፋ ችግርም አልገጠማቸውም። እንደውም ‹‹ዓይነ ሥውር መሆኔ አይታወቀኝም›› ይላሉ ወይዘሮ ዘነበች፡፡

የልጅነት ጊዜያቸው አብቅቶ ወደ አዋቂነት ዕድሜ ከተሸጋገሩ በኃላ ግን አንዳንድ ችግሮችን ማስተዋላቸውን አልሸሸጉም፡፡ ዓይነ ስውር በመሆናቸው ዕቃ ለመግዛት ሲፈልጉ የፈለጉት ዕቃ እንደሌለ ተነግሯቸዋል፡፡ እንዲህ አይነቱ ነገር ሲያጋጥማቸው ፈጣሪያቸውን ‹‹ግን ለምን?›› ብለው ጠይቀዋል፡፡ ታዲያ ወይዘሮ ዘነበች በዚህ ነገር ብዙም አይብሰለሰሉም፡፡ የሰዎች ይህን የሚያደርጉት ባለማወቃቸው ቢሆን ነው ብለው ወደ ሥራቸው ይመለሳሉ፡፡ በጉዞ ወቅት መንገድ ሲስቱ ሰዎች ዝም ማለታቸውንም ታዝበዋል፡፡

ወይዘሮ ዘነበች መምህርት በነበሩበት ወቅት የሚያስተምሩት ዓይናማ ተማሪዎችን ነበር፡፡ ተማሪዎች አብዛኛዎቹን መምህራን እንደሚያስቸግሩ የሚታወቅ ቢሆንም በእርሳቸው ክፍለ ጊዜም ክፍል ለቀው የሚወጡ አንዳንድ ተማሪዎች እንደነበሩ ያስታውሳሉ። ድርጊቱም ከአንድም ሁለት ግዜ አስከፍቷቸዋል። ይህም ያለማወቅ ወይም የግንዛቤ እጥረት መሆኑና ፈጣሪንም ሆነ ሰውን ማማረር እንደማይገባ ይገልፃሉ፡፡

ለወይዘሮ ዘነበች ከሁሉም በላይ ፈተና የሆነባቸው ነገር ቢኖር ልጅ ወልዶ ማሳደጉ ነበር፡፡ ይህንንም ቢሆን በሚገባ አልፈውታል፡፡ መምህርቷ ዛሬ የሦስት ልጆች እናት ናቸው፡፡ ልጆቻቸውን በሚገባ አሳድገው እና አስተምረው ለወግ ማዕረግ አብቅተዋል፡፡ የልጅ ልጅ አይተው ስመዋል፡፡ ያጋጠማቸውን ችግሮች ሁሉ ተቋቁመው ትውልድ በመቅረጽ አሳልፈዋል። ዛሬ ደግሞ ሴት ዓይነ ሥውራን ችግሮችን በጽናት እንዲያልፉ እና የተለያዩ ድጋፍ የሚያደርግላቸውን የበጎ አድራጎት ድርጅት በሥራ አስኪያጅነት እየመሩ ይገኛሉ። ወይዘሮ ዘነበች ፈተናዎችን ተቋቁሞ እና ሠርቶ መቀየር እንደሚቻል ለብዙዎች ከሕይወት ልምዳቸው እንዲማሩ ማድረግ ችለዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ዘነበች ያሉ ዓይነ ሥውራንም ሆኑ ሌሎች አካል ጉዳተኞች በቤተሰባቸው መልካም አስተዳደግ፣ በራሳቸው ብርታትና ጥረት መሥራት እንደሚችሉ በተግባር ማሳየት ችለዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም የተለያየ የአካል ጉዳት ያለባቸው አካል ጉዳተኞች ፈተናዎችን ተቋቁመው ለስኬት እንዲበቁ የተለያዩ የግንዛቤ ሥራዎች መሠራት እንዳለበት ወይዘሮ ዘነበች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም እንደ ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ እና መንግሥታዊ ተቋማት አካል ጉዳተኞችን በመደገፍ ብሎም ለእነርሱ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ስኬታማ እንዲሆኑ ማገዝ እንደሚገባ ይጠቁማሉ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## እስራኤል የተኩስ አቁም ተደራዳሪ ቡድኗን ከዶሃ አስወጣች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እስራኤል የተኩስ አቁም ተደራዳሪ ቡድኗን ከኳታር አስወጣች።

በኳታርና ግብፅ አደራዳሪነት በዶሃ ሲካሄድ የቆየው ንግግር በሃማስ ቅድመ ሁኔታዎች ምክንያት ሳይሳካ መቅረቱን የእስራኤል ባለሥልጣናት ተናግረዋል።

በድርድሩ ላይ ለተሳተፉት የእስራኤል የስለላ ድርጅት ኃላፊ ቅርበት ያላቸው ግለሰብን ዋቢ አድርጎ ሬውተርስ እንደዘገበው፥ እስራኤል በጋዛ የሚገኙት የሃማስ መሪ ያህያ ሲንዋር ድርድሩን እያወኩ ነው በሚል ከሳለች።

ሃማስ በበኩሉ እስራኤል የተኩስ አቁም ድርድሩ እንዲጓተት የምትፈልገው በጋዛ ድብደባዋን ለመቀጠል ነው ሲል ወቅሷል።

እስራኤልና ሃማስ ለስድስት ሳምንታት ተኩስ አቁመው ከ130 የእስራኤል ታጋቾች 40ዎቹ እንዲለቀቁ ነበር ድርድር ሲደረግ የቆየው።

ሃማስ የእስራኤል ወታደሮች ከጋዛ ሙሉ በሙሉ የሚወጡበትና ጦርነቱ የሚቆምበትን እንጂ ጊዜያዊ የተኩስ አቁም ላይ መደራደር እንደማይፈልግ መግለጹ ተዘግቧል።

የፍልስጤሙ ቡድን በጦርነቱ ምክንያት ወደ ደቡባዊ ጋዛ የተፈናቀሉ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱም ጠይቋል።

እስራኤል ሃማስ በጠየቀው ልክ ባይሆንም የተወሰኑ ፍልስጤማውያን ወደ ሰሜናዊ ጋዛ በመመለስና ከ700 እስከ 800 ፍልስጤማውያን እስረኞችን በመፍታት ታጋቾችን ለማስለቀቅ ተስማምታ ነበር።

ይሁን እንጂ ሃማስ ፍልስጤማውያን ተኩስ እንዲቆም እንደማይፈልጉ ያመላከተ “ቅዠት” የሚመስል ቅድመ ሁኔታ አስቀምጧል ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ።

ከዚህ ቀደምም የቡድኑን ቅድመ ሁኔታዎች የሚያጣጥሉት ኔታንያሁ ጦራቸው ከጋዛ እንደማይወጣና ጦርነቱ እንደሚቀጥል የሚያሳይ መግለጫ አውጥተዋል።

በቴልአቪቭ የሚገኙ ከ300 በላይ የታጋቾች ቤተሰቦች በአስቸኳይ የተኩስ አቁም ስምምነት ተደርሶ ታጋቾቹ እንዲለቀቁ በሀገሪቱ የመከላከያ ሚኒስቴር ቢሮ ተቃውሟቸውን እያሰሙ ነው።

እስራኤል የፀጥታው ምክር ቤት በጋዛ በአስቸኳይ ተኩስ እንዲቆም የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ባፀደቀ ማግስት ተደራዳሪዎቿን ከዶሃ አስወጥታለች።

በራፋህ እና በሌሎች ከተሞች እየፈጸመችው ያለው ጥቃትም ይበልጥ እየጨመረ መሄዱን የጋዛ ጤና ሚኒስቴር አኃዛዊ መረጃዎች ያሳያሉ።

## ዘለንስኪ ከፍተኛ የፀጥታ ባለሥልጣንን ከኃላፊነት አባረሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ዘለንስኪ ከፍተኛ የፀጥታ ባለሥልጣንን ከኃላፊነት አባረሩ።

የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ እያካሄዱት ባለው የአመራር ለውጥ ዘመቻ ከትናንት በስትያ የዩክሬንን የብሔራዊ የፀጥታ ምክር ቤት ጸሐፊ ማባረራቸውን እና በእሳቸው ቦታ የውጭ ደኅንነት ኤጀንሲ ኃላፊ የነበሩትን መሾማቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

ፕሬዚዳንቱ ባለፈው ወር ዩክሬን ከሩሲያ ጋር እያደረገች ባለው ጦርነት ቁልፍ ሚና ነበራቸው የተባሉትን ዋና የጦር አዛዥ ከኃላፊነት ማንሳታቸው ይታወሳል።

የፀጥታ ኃላፊው መባረራቸውን ይፋ ያደረገው የፕሬዚዳንቱ ድረ-ገጽ የተባረሩበትን ምክንያት ግን



ግልጽ አላደረገም።

የተሰናበቱት የብሔራዊ ደኅንነት እና የመከላከያ ምክርቤት ፀጥታ ኃላፊው አሌክሲ ዳኒሎቭ ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ ሥልጣን ከመያዛቸው ከአንድ ወር በፊት ከ2019 ጀምሮ ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

ዘለንስኪ ባስተላለፉት የቪዲዮ መልዕክት ዳኒሎቭ አዲስ ኃላፊነት እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል።

ዘለንስኪ ዳኒሎቭን ያነሱበትን ምክንያት አላብራሩም፤ ነገርግን የብሔራዊ ደኅንነታችንን ለመጠበቅ አስተማማኝ የትንበያ አቅም ማሳደግ ያስፈልጋል ብለዋል።

"ዩክሬንን የማጠናከር እና በሁሉም ዘርፎች ያሉ አሠራሮችን የማደስ ሂደት ተጠናክሮ ይቀጥላል" ብለዋል ዘለንስኪ።

ዘለንስኪ በግልጽ የማይታወቁትን የውጭ ደኅንነት ኤጀንሲ ኃላፊ የሆኑትን የ51 ዓመቱን ኦሌክሳንደር ሊቲቪንኮን ምክርቤቱን እንዲመሩት ሹመት ሰጥቸዋል።

ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ አዲሱ ተሿሚ ዩክሬን የምትፈልገውን የደኅንነት እና የፀጥታ ልምድ ያካበቱ ናቸው ብለዋል።

ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ የሆነው ምክር ቤቱ የዩክሬንን ከፍተኛ የፖለቲካ፣ የፀጥታ እና የመከላከያ ኃላፊዎች ያካተተ እና የብሔራዊ ደህንነት ጉዳዮችን የሚያስተባብር ነው።

ፕሬዚዳንቱ ምክትል የወታደራዊ ስለላ ምክትል ኃላፊ የነበሩትን ኦሌህ ኢቫስቸንኮን የውጭ ደኅንነት ኃላፊ አድርገው ሾመዋቸዋል።

የዩክሬን እና ሩሲያ ጦርነት ሁለት ዓመት ያለፈው ሲሆን ሩሲያ በቅርቡ በምሥራቅ ዩክሬን አቭዲቪካን ጨምሮ በርካታ መንደሮችን ተቆጣጠራለች።

ዩክሬን ቦታዎቹን የለቀቀችው የምዕራባውያን ወታደራዊ እርዳታ በፍጥነት ባለመድረሱ እና ወታደሮቿን ከከበባ ለማውጣት መሆኑን መግለጿ ይታወሳል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# በአዲስ መንገድ ወደላቀ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ስኬት

**እስማኤል አረቦ**

የፕሮጀክቶች መጓተት ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትፈተንባቸው ከቆየችባቸው እና የልማቷም ማነቆዎች ሆነው ከዘለቁ ችግሮቿ መካከል አንዱና ዋነኛው ነው:: በተለይም ከለውጡ በፊት በነበሩ ዓመታት ኢትዮጵያ በፕሮጀክቶች መጓተት የምትታወቅና በርካታ የሕዝብ ሃብትም ለኪሳራ ሲዳረግባት የቆየች ሀገር ነች::

ምክንያቱም የፕሮጀክቶች መጓተት ዘርፈ ብዙ ጉዳት አለው:: ለምሳሌ፣ አንድ ፕሮጀክት ሲጓተት፣ በአንድ በኩል ለፕሮጀክቱ የሚወጣው ገንዘብ እየጨመረ ይሄዳል:: በሌላ በኩል ደግሞ ፕሮጀክቱ በወቅቱ ተጠናቅቆ ለሚፈለገው ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ግልጋሎት በመዋል ሊያስገኝ የሚገባውን ጥቅም እንዳያስገኝ ያደርገዋል::

በዚህ ረገድ የሚጠቀሱ አያሌ ፕሮጀክቶች አሉ:: ለአብነት ያህል፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን ብናነሳ፤ ግድቡ በ80 ቢሊዮን ብር ገደማ ወጪ ለመገንባት ውል ቢገባም፤ ከለውጡ በፊት በነበረው ምዝበራና ኋላቀር የግንባታ አካሄድ ግድቡ ከመጓተትም አልፎ ችግሮች ገጥመውትም ነበር::

በዚህም በተጠቀሰው በጀት ተከናውኖ በአምስት ዓመታት ውስጥ ይጠናቀቃል የሚል ትልም ተይዞለት ቢሆንም፤ በአቅምም፣ በአሰራር ብልሹነትም፣ በሌሎችም ምክንያቶች በዓመትም በበጀት ወደ ሦስት እጥፍ፣ በዓመትም እንደዛው ጨምሮ ሳይጠናቀቅ 13 ዓመታትን ዘልቋል:: ይሄ ፕሮጀክት ደግሞ ካለው ከፍ ያለ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ጂኦ-ፖለቲካዊ እንዲሁም ዲፕሎማሲያዊ ፋይዳ አንጻር ሲታይ እንደ ሀገር የሚያሳድረው ተጽዕኖ እጅጉን ከፍ ያለ ነው::

በዚህና መሰል የፕሮጀክቶች መጓተት ምክንያት የሚታይን ችግር እና ችግሩ የሚያሳድረውን ከፍ ያለ ኪሳራ ከማቃለል አኳያ፤ ከለውጡ ማግስት የተወሰዱ ዘርፈ ብዙ ርምጃዎች ትልቅ ውጤት ያሳዩ ናቸው:: ለምሳሌ፣ ቀደም ብዬ የጠቀስኩትን የሕዳሴ ግድብ ጉዳይ ብናነሳ፤ ያሉበትን በርካታ ችግሮች በመፍታት እና አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ዛሬ ላይ ፕሮጀክቶ በ95 በመቶ አፈጻጸም ላይ እንዲደርስም፤ የኤሌክትሪክ ብርሃን ለሕዝቦች ማድረስ እንዲጀምርም አስችሏል::

ይሁን እንጂ ከገንዘብ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ከለውጡ በፊት በነበረው ብልሹ አሰራር ምክንያት በኢትዮጵያ የተለያዩ 102 ፕሮጀክቶች መጓተታቸው ምክንያትም 42 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ ወጪ ጠይቀዋል:: የፕሮጀክቶች መጓተት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ጉዳቶች ያሉት ሲሆን፤ ፕሮጀክቶቹ ከተመደበላቸው በጀት ተጨማሪ ወጪ መጠየቃቸውም አንዱ ነው። በተለይ በብድር የሚሰሩ ከሆነ ተጨማሪ ወለድ እንዲከፈል ያስገድዳሉ፤ ሌላ ብድር ለማግኘትም መሰናክል ይፈጥራሉ። ፕሮጀክቶቹ በወቅቱ ተጠናቀው ይሰጡት የነበረውን ጥቅምም ያሳጣሉ።

ቀደም ሲል በነበረው አሰራር አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች የሚዘገዩት በመንግሥታዊ ውስብስብ ቢሮክራሲ አሰራር፤ ቀና ትብብር ባለመኖር፤ በፕሮጀክት አስተዳደር ችግር እና በዕቅዶች የተፈጻሚነት ጉድለት መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል። ከዚህ ጥናት በኋላ በተወሰደ ርምጃም በኢትጵያ አዲስ የፕሮጀክት አፋጻጸም መመዝገብ ጀምሯል:: አንዳንዶቹ ፕሮጀክቶችም አስገራሚ በሆነ ፍጥነት ተጠናቀው ለአገልግሎት ሲበቁ እየታየ ነው::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጓተቱትም ሆነ አዲስ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ረገድ ብዙ መሻሻሎች ታይተዋል:: የግንባታ ሂደት በሪፖርት ብቻ ሳይሆን በቦታው በመገኘትም ጭምር ያሉባቸውን ተጨባጭ ችግሮች እንዲቀረፉ በማድረግ እና አዳዲስ ፕሮጀክቶችም በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቅ በማድረግ ረገድ ወደ አዲስ የፕሮጀክት አፈጻጸም ምዕራፍ መሸጋገር ተችሏል::

በዚህም ለዘመናት ሲጓተቱ የበሩ ፕሮጀክቶችን

**በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ልዩ የቱሪዝም መስህብ ከማድረጉም ባሻገር የኢኮኖሚያዊ አበርክቶውና የሀገሪቱን ገጽታ ከመለወጥ አንጻር ፋይዳው ትልቅ ነው። ወንጪ ደንዲ የኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት በሕዝብ ትብብር የተሰራ በመሆኑ የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግና ከ12ሺ በላይ ለሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል የፈጠረ ነው**

አጠናቆ ለአገልግሎት ከማብቃት ባሻገር፤ የተጀመሩትን በፍጥነት የማስቀጠልና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በሚገርም ፍጥነት ለውጤት ማብቃት ተችሏል:: ከዓመታት በፊት ተጀምረው በመጓተት ብሎም በመክሰም ሂደት ውስጥ የነበሩትን እንደ ኮይሻ ያሉ ግድቦችንም ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ተችሏል:: የንግድ ባንክን ሕንጻም ከመቆም ታድጎ ለአገልግሎት አብቅቷል:: የሀገር መከላከያ ሰራዊት እና የኢንሳ ዋና መስሪያ ቤቶች አምረውና ደምቀው ለአገልግሎት ክፍት መሆናቸው የዚሁ ጅምሮ በፍጥነት የማጠናቀቅ አብነቶች ናቸው::

በገበታ ለሸገር እና በገበታ ለሃገር የታየው አፈጻጸምም እጅጉን ያስደመመ ነበር:: ለምሳሌ፣ በገበታ ለሀገር ከተገነቡት ፕሮጀክቶች መካከል የወንጪ ደንዲ የኢኮ ቱሪዝም ማዕከል አንዱ ነው። በችግር ውስጥ ተሆኖም በአጭር ጊዜ ውስጥ በዚህ ፕሮጀክት ላይ የታየው አፈጻጸም እንደ ሀገር የደረስንበትን የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ከፍታ የሚናገር ነው::

በፕሮጀክቱ አካባቢውን በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ልዩ የቱሪዝም መስህብ ከማድረጉም ባሻገር የኢኮኖሚያዊ አበርክቶውና የሀገሪቱን ገጽታ ከመለወጥ አንጻር ፋይዳው ትልቅ ነው:: ወንጪ ደንዲ የኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት በሕዝብ ትብብር የተሰራ በመሆኑ የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግና ከ12ሺ በላይ ለሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል የፈጠረ ነው::

የኢኮ-ቱሪዝም ፕሮጀክቱ እስከ 39 ኢኮሎጂዎችና ሌሎች ተጨማሪ የመዝናኛ ስፍራዎችን ያቀፈ ነው። በፕሮጀክቱ ባለ አምስት ኮከብ ሆቴሎች፣ ባህላዊ ሎጅና ሬስቶራንት፣ የአትሌቲክስ መንደር፣ የጎልፍ ክለብ ከመካተታቸውም በሻገር በስፋት በአደጉት ሀገራት የሚገኙ ግዙፉ የአምዩዝመንትና የውሃ ፓርኮችንም የያዘ ነው።

የወንጪ ደንዲ ሃይቅ ዘመናዊ የኢኮ-ቱሪዝም ሎጅ ኢትዮጵያ ያላትን ዕምቅ የተፈጥሮ ሃብቶች በአግባቡ በማወቅ፣ በመጠቀምና በመጠበቅ ለትውልድ የሚተርፍ ስራ መስራት እንደሚቻል ማሳያ ነው:: ኢትዮጵያ እምቅ የሆነ ሀብት ያላት ሀገር በመሆኗ ከመገፋፋትና ከመጣላት ወጥተን ሃብቶቻችንን ማልማት ከቻልን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከድህነት መላቀቅ እንድምንችል የወንጪ ደንዲ ሃይቅ ዘመናዊ የኢኮ-ቱሪዝም ሎጅ አንዱ ማሳያ ሊሆን የሚችል ነው::

አዲሱ አመራር ነባር ፕሮጀክቶችን ከማጠናቀቅ አልፎ፣ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ በመጨረስ የብዙዎችን አድናቆትና ይሁንታ አግኝቷል:: ከእነዚህ ውስጥ ገበታ ሸገር ተብለው ከተጀመሩና ለመዲናዋ መስህብ ከሆኑት ፕሮጀክቶች ውስጥ የአንድነት፤ የወዳጅነትና የእንጦጦ ፓርኮች ተጠናቀው የአዲስ አበባ ድምቀት ሆነዋል:: የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክትም የከታማዋ አንዱ መስህብ ለመሆን በቅቷል:: በገበታ ለሀገር የተጀመሩ የኮይሻ፣ የጎርጎራና የወንጪ ፕሮጀክቶች ሂደታቸውን ጠብቀው በመገንባት ላይ ናቸው::

በአይነቱ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውም የሳይንስ ሙዚየምም በአጭር ጊዜ ተገንብቶ የከተማዋ ድምቀት ሆኗል:: የዓድዋ "00" ኪሎ ሜትር ሙዚዬምም ሌላው የከፍታዋ መልከ ሆኗታል:: አሁን ደግሞ ሙሽራዋ አዲስ አበባ በአዳዲስ ፕሮጀክቶች ብቅ ብላለች:: አዲስ አበባ የዓለም የዲፕሎማሲ መዲና፣ የአፍሪካ ዋና ከተማ፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴ መናኸሪያ እንደ መሆኗ፤ ይህን የሚመጥን ልማት እየተከወነላት ይገኛል:: የልማቱ መጠሪያም የአዲስ አበባ ኮሪደር ልማት ይሰኛል ::

ይህንኑ በማስመልከት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ፣ የኮሪደር ልማቱ በተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎች የተሠሩ ‹‹የሚያማምሩ የልማት ሥራዎችን ማገጣጠም›› እንደሆነ ገልጸዋል:: ‹‹ስታንዳርዱን የጠበቀ ገጽታ፣ ውበት፣ አገልግሎትና ፅዳት ሊኖራት ይገባል፤›› ያሉት ከንቲባዋ፣ አምስት ኮሪደሮችን ያማከለ ልማት መጀመሩን ተናግረዋል:: ባለፈው ዓመት ግንቦት ጨረታው ወጥቶ የተጠናው የኮሪደር ልማት ወደ ትግበራ እንደገባም ተናግረዋል።

ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ እስከ ቦሌ ድልድይ፣ ከቦሌ ድልድይ በመገናኛ ወደ ሲኤምሲ፣ ከቦሌ ተርሚናል ወደ ጎሮ፣ ከሜክሲኮ ወደ ወሎ ሠፈር፣ እንዲሁም ከእንግሊዝ ኤምባሲ ወደ አራት ኪሎ የሚወስዱ ኮሪደሮች መሆናቸው ታውቋል:: ስራውም በስድስት ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቀም ተናግረዋል::

እነዚህ ስራዎች ሲከናወኑም ከተለያዩ ቦታዎች ለሚነሱ ግለሰቦች ምትክ ቦታ እንደሚሰጥ አስተዳደሩ አስታውቋል:: ቀደም ሲል በቀበሌ ቤት ውስጥ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ከቦታው በመነሳታቸው ምክንያት ለችግር እንዳይጋለጡ ምትክ የቀበሌ ቤት ወይም ኮንዶሚኒየም እንደ ምርጫቸው እንደሚሰጣቸው አስተዳደሩ አስታውቋል:: በተመሳሳይም የግል ይዞታ የነበራቸው ነዋሪዎች ምትክ ቦታና ካሳ እንደሚሰጣቸው ተነግሯል::

በአጠቃላይ በአምስት አቅጣጫዎች እየተከናወነ ያለው ኮሪደር ልማት ከተማዋን ከመሰረቱ የሚቀይር ነው:: ከሁሉም የሚያስደስተው ደግሞ ስራውን በታያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ የሚደረገው ርብርብ ነው:: አጠቃላይ ያለውን እንቅስቃሴ ለተመለከተ የኮሪደር ልማቱ በታሰበለት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ መገመት አያዳግትም:: የተሸከርካሪ መሄጃ አስፋልቱን እና የእግረኛ መንገዱን ስፋት ለተመለከተውም ዓለም አቀፍ ደረጃን ባሟላ መልኩ እየተገነባ መሆኑን ያመላክታል::

በአዲስ አበባ የተጀመረው የኮሪደር ልማት ውብና በኢትዮጵያ ልክ የሆነች ዋና ከተማን ለመፍጠር ያለመ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መግለጻቸውም ይሄንኑ የሚያረጋግጥ ነው::: ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንዳሉትም ‹‹በአዲስ አበባ የተጀመረው በርከት ያለ የኮሪደር ልማት ሥራ ውብና በኢትዮጵያ ልክ የሆነች ዋና ከተማን ለመፍጠር ያለመ መሆኑን መገንዘብ ይገባል:: የኮሪደር ልማቱን ለማከናወን ሲባል የማኅበረሰቡን አጥር፣ ቤትና የመሥሪያ ቦታ እያፈረስን ያለነው ከተማዋን በገባነው ቃል መሠረት ለማስዋብና በኢትዮጵያ ልክ የሆነች ዋና ከተማን ለመፍጠር መሆኑን ተገንዝባችሁ የተጎዳችሁ ካላችሁም በይቅርታ መንፈስ ትብብር እንድታደርጉልን እጠይቃለሁ›› ብለዋል::

ያልተገነባ ሀገርና ከተማ ተደጋጋሚ መፍረስ ያጋጥመዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የፌዴራል መንግሥትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመራሮች ተባብረን ስድስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አሁን ያፈረስናቸውን ሥራዎች ጠግነን አዲስ አበባን በገባነው ቃል መሠረት ውብ ለማድረግ ቀን ከሌት እንሠራለን ሲሉም ቃል ገብተዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወደፊቷ አዲስ አበባ በአፍሪካ ደረጃ ውብ የሆነች ከተማ እንደምትሆንም ተናግረዋል:: ‹‹አዲስ አበባ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በአፍሪካ ካሉ ዋና ከተማዎች ከኬፕታውን በስተቀር የሚወዳደራት ከተማ እንደማይኖር በተግባር የምናሳያችሁ ጉዳይ ነው::›› ሲሉ አዲስ አበባ እንደስሟ ውብ እና አዲስ የምትሆንበት ጊዜ መቅረቡን ተናግረዋል::

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በብዙ ነገር ወደ ኋላ ቀርታለች፤ ስለዚህ መፍጠን ያስፈልጋል። ወደ ኋላ ከቀረንባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ ነው። የዶክተር ዐቢይ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ ወዲህ አዲስ አበባን የተዋበችና በቱሪስቶችም ተመራጭ ከተማ ለማድረግ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል::

በአዲስ አበባ የታሪክ ስብራታችንን ለመጠገን በአፍሪካ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን የዓድዋ ሙዚየምን ጨምሮ፣ ፍሬንድሽፕ፣ እንጦጦና አንድነት ፓርክን፣ አብርሆት ቤተ መጻሕፍትን፣ መስቀል አደባባይ እና ሌሎች በርካታ ፕሮጀክቶች ተገንብተዋል:: በተለያዩ አቅጣቻዎች እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶችና በተናጠል ያሉ "ዶቶች" ሲገናኙ አዲስ አበባ እንደ ስሟ ውብ እና አዲስ ከመሆኗም ባሻገር አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ ዋና ከተማ መሆኗንም ማንም አይቶ መመስከር ይችላል::

በአጠቃላይ በአዲስ አበባም ሆነ በተቀረው የሀገሪቱ አካባቢዎች በአጭር ዓመታት ውስጥ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ስራዎች ኢትዮጵያ በብልጽግና ጎዳና እየተራመደች መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው:: እነዚህ ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሚሰሩበት ፍጥነትና ጥራት ደግሞ እጅን አፍ ላይ ለመጫን የሚያስገድዱ ናቸው:: መሽቶ በነጋ ቁጥር ተጀምረው የሚያልቁ ፕሮጀክቶችን ለተመለከተ በፕሮጀክቶች መጓተት ይህቺ ሀገር ምን ያህል ወደ ኋላ እንደተጎተተች ለመረዳት አያዳግተውም::

በፕሮጀክቶች መጓተት ምክንያት ቀደም ሲል ተጀምረው ከንቱ የቀሩት የያዩ ማዳበሪያ፤ የስኳር ፋብሪካዎች፤ የመንገድ ፕሮጀክቶች፤ በየቦታ እንደአሸን ተጥለው የሚገኙ የግንባታ ማስጀመሪያ የመሰረት ድንጋዮች ይህችን ሀገር በብዙ ዋጋ እንድትከፍል ያደረጓት ናቸው:: እነዚህ የተጓተቱ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ገንዘብ የባከኑባቸው ከመሆኑም ባሻገር በከፍተኛ መጠን ባለው ወለድ በተገኘ የውጭ ብድር የተጀመሩ በመሆናቸው ሀገሪቱን እስካሁን ከፍላ ላልጨረሰችው ዕዳ ዳርገዋታል::

አሁን ግን ነገሮች ተቀይረዋል:: ኢትዮጵያ በግጭቶች፣ መከራዎችና ረሃብ ስትፈተን የቆየች ሀገር ብትሆንም፤ አሁን ላይ ግን ካለፈው ትምህርት ወስዳ ሁኔታዎቹን ወደ ዕድል እየቀየረች ያለች ሀገር ነች:: ቀደም ሲል በጦርነት፤ በርሃብና ድርቅ የሚታወቀውን ስሟን የሚለውጡ ስራዎችንም በማከናወን ላይ ትገኛለች::

በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ በግብርና፤ በአረንጓዴ አሻራ፤ በኃይል አቅርቦት እና በቱሪዝም ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራት የሀገሪቱ መጻኢ ዕድል ተስፋ ሰጪ እንደሆነ የሚያመላክቱ ናቸው። በዚህ ላይ በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ረገድ እየታየ ያለው እምርታ ሲጨመርበት የነገዋን ኢትዮጵያ አሻግረን ለመመኘት የሚያነሳሳን ነው::

# ስፖርት



## በዓለም ሃገር አቋራጭ ሻምፒዮና ለስኬት የሚያበቃ ዝግጅት ተደርጓል

ብርሃን ፈይሳ

45ኛው የዓለም ሃገር አቋራጭ ሻምፒዮና ከነገ በስቲያ በሰርቢያ ቤልግሬድ ይካሄዳል፡፡ በዚህ ሻምፒዮና ላይ ተሳታፊ ከሚሆኑት ሃገራት መካከልም የምሥራቅ አፍሪካዎቹ የውድድሩ ስኬታማ ሃገራት ኢትዮጵያ፣ ኬንያ እና ዑጋንዳ ለአሸናፊነት ጠንካራ ግምት ተሰጥቷቸዋል፡፡ በሻምፒዮናው ኢትዮጵያን የሚወክለው የአትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድን እንደተለመደው በውጤታማነት ለመመለስ ዝግጁ መሆኑን በሽኝት መርሐ ግብሩ ላይ አስታውቋል፡፡



በሃገር አቋራጭ ሻምፒዮናው የሚሳተፈው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ልዑክ፤

በሃገር አቋራጭ ውድድሮች በውጤታማነታቸው ከሚታወቁ ሃገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ መሆኗ ይታወቃል፡፡ ለዚህም በተያዘው ወር መጀመሪያ አንስቶ ቡድኑ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ መም፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሜዳ፣ በእንጦጦ ዳገታማ ስፍራ፣ ለገጣፎ እና ቃሊቲ አካባቢዎች ዝግጅቱን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በ10 ኪሎ ሜትር አዋቂ፣ በ8 እና 6 ኪሎ ሜትር ወጣቶች (ከ20 ዓመት በታች) እንዲሁም በድብልቅ ሪሌ በሚደረጉት ውድድሮች፤ በእያንዳንዱ ርቀት ከተጠባባቂ ጋር 7 አትሌቶችን እንዲሁም በድብልቅ ሪሌ 4 አትሌቶችን ከ2 ተጠባባቂዎች ጋር ወደ ስፍራው ለማቅናት ተዘጋጅተዋል፡፡

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከትናንት በስቲያ ምሽት በተደረገው የብሔራዊ ቡድኑ የሽኝት መርሐ ግብር ላይ አትሌቶች እንዲሁም አሠልጣኞቻቸው በአካል እንዲሁም በሥነልቡና ዝግጁ መሆናቸውንና በግልና በቡድን ስኬትን ለማስመዝገብ ወደስፍራው እንደሚያቀኑ አስታውቀዋል፡፡

በዚህ ውድድር እጅግ ተጠባቂ ከሆኑ ርቀቶች መካከል አንዱ የአዋቂ ወንዶች 10 ኪሎ ሜትር ሲሆን፤ በተለይ በዑጋንዳ እና ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል ለአሸናፊነት የሚደረገው ትንቅንቅ አጓጊ ነው። አምና በዚህ ሻምፒዮና ላይ ተሳታፊና የሜዳሊያ ባለቤት የነበሩት አትሌቶች ዘንድሮም በቤልግሬድ መሮጣቸው ደግሞ አጓጊነቱን ጨምሮታል፡፡ ባለፈው ዓመት በአውስትራሊያ ባትረስ የብር ሜዳሊያ ያጠለቀው ወጣቱ ኢትዮጵያዊ አትሌት በሪሁ አረጋዊ ለአሸናፊነት ቅድመ ግምቱን ሲያገኝ፤ ዝግጅቱም ይህንኑ እውን ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ይጠቁማል፡፡

ቀሪው ጉዳይም ለሳምንታት በቆየው የዝግጅት ጊዜ በአሠልጣኞቻቸው የተሰጣቸውን መመሪያ እንዲሁም እንደ ቡድን የተደረገውን ሁለገብ ዝግጅት ተግባራዊ በማድረግ በተፎካካሪነት ውጤት ማስመዝገብ እንደሆነም አትሌቱ ጠቁሟል፡፡ ፈታኝ ተፎካካሪዎች መኖራቸው ውድድሩን እጅግ ከባድ እንደሚያደርገው የሚጠበቅ ሲሆን፤ ቡድኑ ፈተናዎችን ተቋቁሞ ለማለፍ የሚያስችል ዝግጅት ማድረጉ ተገልጿል፡፡ ዓመቱ የኦሊምፒክ እንደመሆኑም ከዚህ ውድድር ባለፈ አቅሙን በሌሎች ርቀቶች ላይም መድገም የወጣቱ አትሌት በሪሁ እቅድ ነው «በርካታ ውድድሮች ላይ በመሳተፍ በርካታ ልምዶችን ማካበት ችያለሁ፤ ከዚህ በፊት የተሸነፍኩባቸው ውድድሮች ጭምር ትምህርት ሆነውኛል፡፡ በመሆኑም ያለፈውን ስህተቴን በማረም ውጤታማ ለመሆን ጥረት አደርጋለሁ» ይላል፡፡

በአሠልጣኞች ቡድን አትሌቶችን ሲያዘጋጁ ከቆዩት መካከል ኮማንደር ቶሌራ ዲንቃ አንዱ ሲሆን፤ አትሌቶች በጥሩ ጤንነትና በቅንጅት ዝግጅታቸውን ሲያካሂዱ እንደነበረም ይጠቁማል። ውድድሩ በቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ እንዲሁም ጠመዝማዛ በሆነ የውድድር ስፍራ የሚደረግ በመሆኑ ዝግጅቱም ይህንን እንዲያማክል ማለዳ ከ11 ሰዓት ጀምሮ እንደ እንጦጦ ባሉ ከፍተኛ ስፍራዎች ሲደረግ ቆይቷል፡፡ እንደአጠቃላይም ቡድኑ ጠንካራ አትሌቶችን ያቀፈ መሆኑ ውጤታማ ሆኖ እንዲመለስ እንደሚያስችለውም ያመላክታል፡፡

በአዋቂ ቡድኑ የተካተቱ አትሌቶች ልምድ ያላቸው ሲሆኑ ጠንካራ ተፎካካሪ ከሆኑት የዑጋንዳ እና ኬንያ አትሌቶች ጋርም በምን መልኩ መወዳደር እንደሚገባ ከምንጊዜውም በተሻለ ዝግጅት ተደርጓል፡፡ በወጣቶች በኩልም በቅንጅት ውጤታማ ለመሆን የሚያስችል ዝግጅት የተደረገ ሲሆን፤ በድብልቅ ሪሌም በቱኒዚያ በተደረገው የአፍሪካ ሃገር አቋራጭ ሻምፒዮና ተሳትፈው አቅማቸውን ያሳዩ ወጣት አትሌቶችን ለማሳተፍ ታቅዷል፡፡ በአሕጉር አቀፉ ሻምፒዮና በወጣቶች አብዛኛዎቹን በማሳተፍ አቅማቸውን መፈተሽና ለቤልግሬድ አስተማማኝ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ምናልባትም በአዋቂ ሴቶች አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች የማራቶን አትሌቶች በመሆናቸውና በሃገር አቋራጭ ውድድሮች ልምድም ስለሌላቸው ሊፈተኑ ይችላሉ የሚለው ግን ስጋት እንደሚሆን ነው አሠልጣኙ ያስረዱት፡፡

ስመጥርና ተተኪ አትሌቶችን ያቀፈው የኢትዮጵያ ሃገር አቋራጭ ብሔራዊ ቡድን ስኬታማ ሊያደርገው የሚችለውን ጠንካራ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል። ይሁንና ከጉዞ ጋር በተያያዘ የቡድኑ አባላት ቪዛ ለማግኘት አስቸጋሪ ሁኔታዎች የገጠሙት ሲሆን፤ የሰርቢያ ኤምባሲ በኢትዮጵያ አለመኖር ደግሞ ችግሩ በቀላሉ እንዳይፈታ አድርጎታል፡፡ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም ኬንያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩልም መፍትሔ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ፌዴሬሽኑ አሳውቋል፡፡


## የጨረታ ማስታወቂያ

የጋሞ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ለዞኑ ሴክተር መ/ቤቶች በ2016 በጀት አመት ሎት-1) በጋሞ ዞን ስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራዝ ልማት መምሪያ በጨንቻ ከተማ ሞዴል አንድ ማዕከል ለማስገንባት እና ሎት-2) የጋሞ ዞን መንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ የወጋ መፅሔት ህትመት ሎት-3) የጋሞ ዞን ትምህርት መምሪያ የተማሪ ካርድ ህትመት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ አሳውጆ ለመግዛት ይፈልጋል፡-

**በዚሁ መሠረት፡-**

1) ለሎት-1) ደረጃቸው BC/GC 7 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተቋራጮች ሆነው የሕጋዊነት መረጃ ከሚመለከተው ኮንስትራክሽን ባለስልጣን በ2016 በጀት ዓመት የተመዘገቡ ወይም የብቃት ማረጋገጫቸውን ያሳደሱ እና የ2015 በጀት አመት በኦዲተር የተረጋገጠ ግብር የከፈሉበትን ክሊራንስ ከገቢዎች ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ እንድሁም በሁለቱም ሎት በዘርፉ የታደሰ ንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (TIN NO) ያላቸው፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እና ለአቅራቢነት በegp የተመዘገቡ፡፡
2) የሎት-(1) ማንኛውም ተጫራቾች ከውድድሩ በፊት የሥራ ሳይቱን በራሱ ወጪ አይቶ ከጨንቻ ከተማ አስተዳደር ስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት ሳይቱን ስለማየቱ ማረጋገጫ ደብዳቤ በኦሪጅናል ቴክኒካል ሰነድ ውስጥ አስገብቶ ማቅረብ ይኖርበታል።
3) የሎት-(1) ተጫራቾች አስፈላግውን የግንባታ ዕቃና መሳሪያዎችን በራሳቸው ማቅረብ የምችሉ፡-
4) የጨረታ ማስከበሪያ BID Security - ሎት-(1) 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ለሎት(2ና3) 10,000(አስር ሺህ) ብር በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ (CPO) (በጥሬ ገንዘብ) ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራንቲ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5) ተጫራቾች ሕጋዊ ፈቃዳቸውንና የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) የተመዘገቡበትን ሠርተፍኬት በማቅረብ የጨረታውን ዶክመንት ይህ ማስታወቂያ አየር ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ ለሎት-1 እስከ 21(ሃያ አንደኛው) ተከታታይ ቀናት የማይመለስ ብር 300(ሦስት መቶ ብር) ለሎት(2ና3) እስከ 15(አስራ አምስተኛው) ተከታታይ ቀናት የማይመለስ ብር 100(አንድ መቶ ብር) በጋሞ ዞን ፋይናንስ መምሪያ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000038613263 በማስገባት እና የባንክ አድቫይስ ይዘው ከጋሞ ዞን ገቢዎች መምሪያ ደረሰኝ በመቁረጥ ከዞኑ ፋይናንስ መምሪያ ግዥና ን/አስ/ ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 5 ቀርበው ደረሰኙን በማሳየት የጨረታ ሰነድ መውሰድ ይችላሉ፡፡
6) ተጫራቾች ለሎት-(1) የፋይናንሻል ጨረታ ሰነዱ ተሞልቶ አንድ ኦርጅናልና ሁለት ፎቶግራፊክ ኮፒው በተለያዩ ፖስታ ታሽጎ ኦርጅናልና ኮፒ ተብሎ እላዩ ላይ ተጽፎበት ፡ በሶስቱም ፖስታዎች ላይ ስም ፣ አድራሻና የፕሮጀክቱ ስም በመጻፍ ሕጋዊ የሆነ ማህተም በማሳረፍና በመፈረም እንዲሁም- የህጋዊ ተክኒካል ሰነዶችን አንድ ኦርጂናል ሁለት ፎቶግራፊክ ኮፒ በተለያዩ ፖስታ ከላይ በተገለጸው በተመሳሳይ ሁኔታ ታሽጎ እና ሁሉንም ፖስታዎች በአንድ እናት ፖስታ እላዩ ላይ ማህተም ፡ አድራሻና ስም ጽፎ በመፈረም አሽጎ ለሎት(2ና3) የፋይናንሻል ጨረታ ሰነዱ ተሞልቶ እና የህጋዊ ተክኒካል ሰነዶችን በፖስታ አስገብቶ የጨረታውን አይነት ጽፎ እላዩ ላይ ማህተም አድራሻና ስም ጽፎ በመፈረም አሽጎ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለሎት(1) እስከ 22ኛው ተከታታይ ቀን እና ለሎት(2ና3) እስከ 16ኛው ተከታታይ ቀን 4፡00 ሰዓት ድረስ በጋሞ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ግዥና ን/አስ/ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 5 ለዚሁ በተዘጋጅው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ዘውትር በስራ ሰዓት ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
7) ጨረታው ሎት-(1) በ22ኛው (ሃያ ሁለተኛው) ሎት-(2ና3) በ16ኛው(አስራ ስድተኛው) ቀን በ4፡00 ሰዓት ታሽጎ ልክ በ4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ ዕለቱ የስራ ቀን ካልሆነ በቀጣዩ የስራ ቀን በተመሳሳይ ቦታና ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡

የተጫራቾች አለመገኘት ጨረታውን ከመከፈት አያስተጓጉልም፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፍል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ በጋሞ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ስልክ ቁ 046-881-3338 ይደውሉ፡፡**

**የጋሞ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ለዞኑ ሴክተር መ/ቤቶች**